# ፯

## ይዘቱን መቆጣጠር

### መጽሐፍ ቅዱስን በተለያየ መንገድ ማንበብ

ከቅዱሳት መጻሕፍት መካከል አንደኛውን የምናብራራ ወይም በአንድ ርእስ ጉዳይ ላይ የምንሰብክ ከሆነ መልእክቱን በተለያዩ አቀራረቦች ልንመለከተው ይገባል:: ከቅዱሳት መጻሕፍት አንድን ምዕራፍ አውጥተን በምናብራራበት ጊዜ÷ ምዕራፉን በሙሉ በማንበብ መጀመር አያስፈልገንም:: በአንድ ርእስ ላይ ለመስበክም÷ የግድ አንድ የተመረጠ ክፍል ማንበብ አይኖርብንም:: አስፈላጊው ነገር÷ አድማጮቻችን በሐሳባቸው መጽሐፍ ቅዱስን መመርመርና ማሰላሰል እንዲችሉ ዕድሉን መክፈት ነው::

በምንሰብክበት ጊዜ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሳይከታተሉ÷ ቁጭ ብለው አድማጮች ብቻ ከሆኑ÷ ይህን ልምዳቸውን እንዲተው ለማድረግ መጣር ይገባናል:: ሊያደርጉት ይገባል ብለን የምናምንበትን ተግባርም ፊት ለፊት÷ በታማኝነት መግለጽና ማስረዳት አለብን:: መጽሐፍ ቅዱስ ስብከት አይደለም፤ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ዓላማችንም የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ነው:: በመሰበኪያው መድረክ ላይ ያለነው÷ በቀላሉ በስብከታችን ተይዘው እንዲቆዩ ለማድረግ ብቻ አይደለም፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውን ይዘው እንዲመጡ እናበረታታቸዋለን፤ በዚህም ሁኔታ በተደጋጋሚ ሲመጡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት ጋር በሚገባ ይተዋወቃሉ::

ስለ መርሐ ስብከት ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል፤ የዚህ መጽሐፍ ብቸኛ ዓላማ ግን እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን በሰጠበት ሁኔታ እንዴት አብራርቶ መስበክ እንደሚቻል ለማመልከት ነው:: በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ የስብከት ዐይነቶች ጠቃሚዎች ናቸው፤ ይሁን እንጂ በርእስ ጉዳዮች ላይ መነጋገር የዚህ መጽሐፍ ዓላማ አይደለም:: ያም ሆነ ይህ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ አስቀድመን የጠቀስን ስለ ሆነ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦች ለስብከት ከተመረጡ አርእስቶች ጋር ስላላቸው ግንኙነት እንመለከታለን::

ምንም እንኳን አድማጮቻችን የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአንድ በተለየ ርእስ ላይ የሚናገሩትን ራሳቸው ተከታትለው እንዲረዱት ብንፈልግም በርካታ ማጣቀሻዎችን በመጥቀስ ግራ እንዳናጋባቸው መጠንቀቅ አለብን:: ተዛማጅነት አለው የምንለውን ጥቅስ ሁሉ አንብበን ማዳረስ አንችልም፤ ሆኖም ቍልፍ የሆኑትን ጥቅሶች ማንበብ እንችላለን:: ሌሎችን ግን በቃላችን እንጠቅሳለን ወይም በስብከት ማስታወሻችን ጽፈን እንይዛቸዋለን:: አድማጮቻችንን በስብከት

ማስታወሻችን ውስጥ የተጻፉትን ጥቅሶች በሙሉ ወይም በክፊል አብረውን እንዲመለከቱ በማድረግ ልናሳትፋቸው እንችላለን:: ነገር ግን እየደጋገሙ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በመክፈት አንዴ ወደ ፊት፥ ሌላ ጊዜ ወደ ኋላ እንዲመለሱ ብናስቸግራቸው ርጋታ እናሳጣቸውና ተበሳጭተው ማዳመጣቸውን እንዲተው ይገፋፋሉ:: በተደጋገሚ ጥቅስ የማውጣቱ ተግባር የስብከቱን ፍሰት ያደናቅፈዋል::

በአንድ ርእሰ ነገር ላይ የምንሰብክ ወይም በአንዱ መጽሐፍ ላይ ማብራሪያ የምናቀርብ ብንሆንም፥ በማንኛውም ሁኔታ አቀራረባችን ከሁኔታዎች ጋር የሚስማማበትን መንገድ ማፈላለግ ይጠበቅብናል:: ለውጥ የማድረግ እንቅስቃሴው ግብታዊ አይሁን:: መሆን ያለበት አድማጮች በሚጠባበቁትና ሊከተሉት በሚችሉት ዘዴና መንገድ ነው::

## እጅግም አይብዛ፤ በጣምም አይነስ

ስብከትን በተመለከተ ያለብን ችግር ስብከታችን ሊይዘውና ሊተወው የሚገባ የሐሳብ መጠን ላይ የምናደርገው ውሳኔ ነው:: ይህን ለመወሰን ለስብከት ከመረጥነው ርእሰ ጉዳይ በመነሣት በስብከቱ ዓላማ፥ የሰባኪው ችሎታ፥ የጉባኤው ፍላጎት፥ ለስብከት የሚመደበው ጊዜ መጠንና ሌሎችም ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው:: ሆኖም ያጠናነውንና ያጠናቀርነውን ሐሳብ በሙሉ ለአድማጮቻችን መድረስ አለበት ብለን ስንወስን፥ ይህ ውሳኔያችን ሊያስከትለው የሚችለውን አደጋ ልንዘነጋ አይገባም::

በዚህ ረገድ፥ ይህን መሰል ስበከት በተለይም ገና የትምህርተ መለከት ሥልጠናቸውን ለፈጸሙ አዲስና ወጣት ሰባኪዎች አደገኛ ነው:: ምክንያቱም በሥልጠናው ጊዜ ያካበቱትን ዕውቀት ሁሉ ለመስበክ ትኩስ የሆነ ፍላጎት ስላላቸው በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ ይህን ማድረግ ይሻሉ:: ይሁን እንጂ ይህን የሚመኙ ሠልጣኞች ስብከቱን እንደተመኙት በተሳካ ሁኔታ ለአድማጮች ማቅረብ አይችሉም፤ የዚህ ምክንያቱ፥ ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በቅርቡ የኮሌጅ ትምህርታቸውን የፈጸሙ ይሁኑ አይሁኑ፥ ወይም ትምህርታቸውን ፈጽመው ወንበር የያዙ በሳል መምህራን ይሁኑ፥ ሁሉም ትኩረታቸው በስብከቶች ስልታዊ የአቀራረብ ዘይቤ ላይ ነው፤ ከዚህ የተነሣ ስብከቶቻቸው ለአብዛኞዎቹ ምእመናን አሰልቺዎች ይሆናሉ:: በአጠቃላይ ሰዎች ለምሳሌ:- ማቴዎስ ወንጌሉን በዕብራይስጥ ወይም በግሪክ ቋንቋ ቢጽፍ ባይጽፍ ግድ የላቸውም:: ስለዚህ ሰባኪዎች እነዚህን የመሳሰሉ ዝርዝር ነጥቦችን አንሥተው ሌላም ጨምረው ሲያመሳክሩ አድማጮችን ግራ ስለሚያጋቧቸው መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

እነዚህን የመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያዎች ሊቀርቡ የሚችሉባቸው መድረኮች አሉ፤ በመደበኛው የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ ግን ይህ መሆን የለበትም:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዋና ትኩረታችን፥ በቤተ ክርስቲያን

ውስጥ በሚደረጉ ቋሚ የሕዝብ ስብሰባዎች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን ይዘት እንዴት ማብራራት እንደሚቻል ማመልከት ነው:: ይህን ተግባር በምንፈጽምበት ጊዜ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕየወታቸው ይገነባሉ፤ ቤተ ክርስቲያንም ትጠነክራለች:: በእርግጥ፥ የአድማጩን የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ማሳደግ እንፈልጋለን፤ ነገር ግን በመደበኛው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የምናቀርባቸውን ስልታዊ ዝርዝር ሐሳቦች ለማቅረብ ጊዜው አይፈቅድም:: ከፋቱ፥ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ይህን ማሳሰቢያ እንደ ምክንያት ቈጥረው ከቶውንም ማብራሪያዊ ስብከት ፈጽሞ እንደሌለ ያስባሉ:: ማሳሰቢያውን የሰጠንበት ዓላማ ግን ከዚህ የተለየ ነው:: ቤተ ክርስቲያንማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያ ያለበት ስብከት በጥቂቱ ሳይሆን በሰፊው ያስፈልጋታል:: መጽሐፍ ቅዱስን አብራርቶ የሚያቀርብ የስብከት ዝግጅት ግን የአድማጩን ስብጥር ከግምት ውስጥ አስገብቶ በሚደረግ ጥናት የሚዘጋጅ ሊሆን ይገባል::

ጳውሎስ በኤፌሶን 4፥11-13 እንዳስተማረው፥ የመጋብያንና የመምህራን ስጦታዎች ሊለያዩ በማይችሉበት ሁኔታ የተሳሠሩ ናቸው:: መምህሩ መጋቢ፥ መጋቢውም መምህር ነው፤ በስብከታችን ውስጥ እነዚህን የአገልግሎት ሚናዎች ማጣመር ይኖርብናል:: ሕዝቡ ከአገልጋዮቻቸው የሚፈልጉትን መጋብያዊ አገልግሎት አስመልክተን መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር አለብን፤ ከዚህም የተነሣ በእምነት፥ በዕውቀትና በብስለት ያድጋሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች ሕይወት ምን ማለቱ እንደ ሆነ እናብራራላቸዋለን፤ የመልእክቱ ዋና ዓላማ ከሕይወታቸው ጋር ስላለው ግንኙነትም እናሳውቃቸዋለን::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንሰብክ ዓላማችን በዚያ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ የምናስተምረውን ክፍለ ምንባብ ወይንም አንድን መጽሐፍ በሙሉ እንዲያውቁ መሆን የለበትም:: በመጀመሪያ ደረጃ የምናስተምረው ከሚሰሙት ጥቅም እንዲያገኙ ለማድረግ፥ ሁለተኛ በራሳቸው እያጠኑ ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ዕድል ለመሥጠት ሊሆን ይገባል::

## በጥንቃቄ ማቀድ

መጽሐፍ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማብራራት ማስተማር የምንችልበት ተአምራዊ ዘዴ አይኖርም:: ለዚህ በጣም አስፈላጊው ነገር ከምናስተምረው ቃል ጋር በበቂ ሁኔታ መተዋወቅ ነው:: የምናስተምረውን ክፍል ጠለቅ ብለን ማወቅ ይኖርብናል፤ ከዚያም፥ በጥንቃቄ ያካበትነውን ዕውቀት፥ ነጥቡን ሁሉ በስብከቱ ከማካተት ይልቅ ለወቅቱ ትምህርት ይጠቅማል የምንለውን ፍሬ ሐሳብ ብቻ መርጠን ሌላውን ለማስቀረት ልንጨክን ይገባናል:: በዚህ ሁኔታ በስብከታችን ውስጥ የሚካተተው ክፍል የስብከታችን መክፈቻ ሊሆን ከመቻሉም በላይ አድማጮቻችን መልእክቱን ተቀብለው እንዲጠቀሙበት ይረዳቸዋል፤ ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ መልእክት ይሆናል::

አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በስድስት ግማሽ ሰዓቶች ከፋፍለን የማብራራት አገልግሎት አለን እንበል፤ ክፍሉን በሚገባ ለማጥናት በርከት ያሉ ጊዜያት ሊወስድብን ይችላል:: ይህን ጥናት ስናካሄድ የምናጠናቅረው ማስታወሻ በምዕራፍ አምስት ውስጥ በተነጋገርነው መሠረት ይሆናል:: ይህን መንገድ ተከትለን ስናጠና ከመጽሐፉ ይዘት ጋር በሚገባ መተዋወቅ እንችላን፤ በአንጻሩም በስብከታችን ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉትን ሐሳቦች እንዴት ልናስፋፋቸው እንደምንችል ጥበቡ ይኖረናል:: እነዚህ ድርጊቶች የመጽሐፉን መልእክት ለመተርጐምና በምንሰብክበት ጊዜ ሐሳቦቻችንን እንዴት በተግባር ላይ ማዋል እንደምንችል ይረዱናል:: እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ትልቁ ችግር የሚገጥመን:: ስብከት የምናቀርብላቸውን ሰዎች ሳናሰለቻቸው፥ በአኳያው ከምንሰብከው ጭብጥ ጋር ሳይያያዝ ላይ ላዩን የሚዳስስ ስብከት ከማሰማት ተጠብቀን፥ የመረጥነውንና በስብከታችን ውስጥ ያካተትነውን ሐሳብ ካለን ጊዜ ጋር መጥነንና አስማምተን መስበክ እንዴት እንችላለን::

ልንናገርበት የተመደበልን ሰዓት ስድስት ክፍለ ጊዜ ቢኖረው፥ በመጀመሪያ ማድረግ ያለብን፥ መጽሐፉን ራሱን በቻለ ስድስት ክፍል መክፈል ነው:: ምናልባት፥ የምንናገርበት ሐሳብ ተከታታይነት ይኖረዋል፤ አድማጮቻችን በየሳምንቱ ሊለዋወጡ ይችላሉ፤ ስለሆንም ያልነበሩት ሰዎች ስለተሰበከው ስብከት ግንዛቤ እንዲኖራቸው የተሰበከውን ፍሬ ሐሳብ በመከለስ ወደዚህኛው ስብከት መግባት እንደሚገባን ማሰብ አለብን::

የሚቀጥለው ተግባራችን ለእያንዳንዱ ስብከት የምናደርገውን ክፍል መወሰን፥ ለምናቀርበው መልእክት የሚጠቅሙንን ክፍለ ምንባቦችም ለይተን መምረጥ ይሆናል:: እነዚህም ክፍሎች ወይንም ቍጥሮች አስተያየት የምንሰጥባቸውና አድማጮቻችን እንዲያነቧቸው የሚጋበዙባቸው ናቸው:: እነዚህ የተመረጡ ክፍሎች፥ ማብራሪያ የምንሰጥባቸው፥ ተግባራዊ የሚሆኑባቸውን መንገዶች የምንጠቁምባቸው፥ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት የሚወክሉ ናቸው::

እነዚህን ክፍሎች በምንመርጥበት ጊዜ ድርጊታችንን ከሁኔታዎች ጋር ማስማማት አለብን:: የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት፥ በተለይም አጭሩን መጽሐፍ በተመለከተ በእያንዳንዱ ቍጥር ላይ ማብራሪያ መስጠት እንችል ይሆናል:: የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት፥ በተለይም ረጅሙን በተመለከተ በአማካይ ማብራራት የምንችለው ጥቂት ክፍሎችን ነው:: ስለዚህም የምናነባቸውንና የምንተዋቸውን ክፍሎች መወሰን አለብን:: ስንት የጥቅስ ክፍሎችን ማንበብ እንደምንችል ለመወሰን፥ አጠቃላይ መመሪያ ከስብከቱ ጊዜ ጋር ሊስማሙ የሚችሉትን ተመሳሳይ ክፍሎች መርጦ መያዝ ነው:: በዚህ መሠረት ለሠላሳ ደቂቃ ስብከት ሠላሳ ጥቅሶችን ወይም ክፍሎችን ልንጠቀም እንችላለን:: ከእነዚህ ጥቂቶቹ ተከታታይ የሆኑ ስብስብ ጥቅሶች ወይም ክፍሎች ሊሆኑ ይችላሉ:: ሌሎች ደግሞ

ከተለያዩ ስፍራዎች የሚጠቀሱ ይሆኑ ይሆናል:: በአጠቃላይ ግን ከመጽሐፉ ማብራሪያ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው::

አብዛኛዎቹ ዘመናውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ኅትመቶች በመጽሐፉ ወይም በምዕራፉ ዋና ከፍሎች ሥር ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው፤ እነዚህ ንዑሳን ክፍሎችም የመጽሐፍ ቅዱስን ልዩ ልዩ ማስረጃዎች እንዴት ማካተት እንደምንችል ለማቀድ ይረዱናል:: የሚቻል ከሆነ አንድን ምዕራፍ ቊጠር በቊጥር ከመበጣጠስ ይልቅ ቊጥሮቹን ጠቅለል አድርገን ማጥናትና ማዘጋጀት ያሻል:: ይህን በምናደርግበት ጊዜ የጸሐፊውን ሐሳብ ተከትለን መሄድ እንጂ ከርእስ ነገሩ ውጪ በመውጣት ወደ ሌላ ጉዳይ መግባት አይገባንም:: ዓላማችን የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍል ለመለስተኛ ስብከት ዝግጅት ርእሶችን እንዲያስገኝልን መጠቀም ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍል በመክፈት የስብከቱ አካል እንዲሆንልን ነው:: አድማጮቻችን ከስብከቱ ክፍል ጋር እንዲተዋወቁ የምናደርግበት ምክንያት፥ የክፍሉን ትርጉምና ጥቅም ተገንዝበው የሚነገራቸውን ማስተዋል እንዲችሉ ነው::

## ውጤታማ ምሳሌዎች

መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ መጻሕፍትን ከአጻጻፋቸው ሥነ ጽሑፋዊ ዘይቤ ጋር አካቶ ይዟል፤ እነዚህን ልዩ ልዩ መጻሕፍት እንደየባሕርያቸው ልናነባቸው ይገባል:: በዚህ ጠባብ ስፍራ ስለ እያንዳንዱ መጽሐፍ የአጻጻፍ ዐይነት ዝርዝር ማብራሪያ ምሳሌ መስጠት አይቻልም:: ስለዚህም ራሳችንን በአራት ምሳሌዎች ላይ መወሰን አለብን:: እነዚህን አራት ምሳሌዎች በሚከተሉት አራት ምዕራፎች ውስጥ እናገኛቸዋለን:: በእያንዳንዱ ሁኔታ የስብከቱ ርዝመት ግማሽ ሰዓት መሆኑን ልብ ማለት ያሻል፤ ንባባችንንም ሆነ ማብራሪያችንን በሠላሳ ደቂቃዎች ውስጥ መወሰን አለብን::

በምዕራፍ ስምንት ውስጥ የብሉይ ኪዳንን ታሪካዊ መጽሐፍ እንመለከታለን፤ ይህም መጽሐፈ መሳፍንት ነው:: ዓላማውም የተወሰኑ ክፍሎችንና ጥቅሶችን በመምረጥ እንዴት አድርገን የብዙ ምዕራፎችን ይዘት ማስተማር እንደምንችል ለማብራራት ነው:: ለአድማጮቻችን ታሪክን ብቻ አንተርክላቸውም፤ በዚያ ፈንታ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትምህርት እንዲገነዘቡና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዴት ተግባራዊ ሊያደርጉት እንደሚችሉ ማስገንዘብ ነው:: አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት (ከዘፍጥረት- ዘዳግም) ያሉትን በተመሳሳይ ልንመለከታቸው እንችላለን፤ እንዲህ ማለትም የትረካ ክፍላቸውን ብቻ ሳይሆን የሕግና የመመሪያ ስብስቦችን የጨምራል::

ቀጥለን አንድን የብሉይ ኪዳን ነቢይ እንመለከታለን:: ምክንያቱም የነቢያቱ ጽሑፎች ትረካዊ መንገድን ሳይሆን የስብከቶች ዘይቤዎችን የሚከተሉ፥ ከስድ ንባብ ሥነ ጽሑፍ ይልቅ ሥነ ግጥማዊ ወይም ቅኔያዊ አጻጻፍ ያላቸው

ናቸው፤ ለመረዳትም እንደ ታሪክ መጻሕፍት ቀላል አይደሉም። እንደዚሁም አብዛኛዎቹ ሰዎች ይዘቶቻቸውን አይረዱም፤ ስለዚህ ምንባቡን ሰፋ አድርገን መግለጽ አለብን። ደቂቅ ነቢያትን በቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብር ውስጥ አስገብተን ማስተማር እንችላለን፤ ምክንያቱም እነዚህ መጻሕፍት አጫጭር ስለ ሆኑ ነው። እንደ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስና ሕዝቅኤል ያሉትን ትላልቅ መጻሕፍት ለማብራራት ግን ዕድሉ የጠበበ ነው።

ስለዚህ በምዕራፍ ዘጠኝ ውስጥ እንደ ምሳሌ ማስረጃ ያቀረብነው ከትላልቆቹ የትንቢት መጻሕፍት ውስጥ አንዱን የኢሳይያስን መጽሐፍ ነው። ትላልቅ መጻሕፍትን እንዴት እንደምናስተምር ዘዴውን ካወቅን ትናንሾቹን መጻሕፍት በማስተማር ረገድ አንቸገርም። በተመሳሳይ ስልት ወይንም ዘዴ ትናንሽ የመዝሙራትንና የጥበባት መጻሕፍትን ማስተማር እንችላለን።

የሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች አዲስ ኪዳንን የሚመለከቱ ናቸው። እዚህ ላይ አድማጮቻችንን ብንመዝናቸው ከብሉይ ኪዳን ይልቅ ከአዲስ ኪዳን ክፍሎች ጋር የሚተዋወቁ ሆነው እናገኛቸዋለን፤ ሆኖም ክፍሎቹን በሙሉ ይገነዘባሉ ማለት አይቻልም። የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች በጣም የተቀራረቡና እምቆች ናቸው። እንደ ብሉይ ኪዳን ጽሑፎች ረጂም፥ ተራኪ፥ ክርክር፥ ገለጻ፥ ውይይትና ምልልስ ያሉባቸው አይደሉም። አብዛኛዎቹ ክፍሎች ከጸሓፊው ሐሳብ ጋር የተወሳሰቡ እምቅ ስለሆኑ ሰፊውን ክፍል በቀላሉ ገረፍ አድርገን ማለፍ አንችልም። በጠቅላላው የጽሑፎቹን ክፍሎች በዝርዝር ማጥናት አለብን። አድማጮቻችንን በየሳምንቱ በእነዚህ ሐሳቦች ላይ ያልተቋረጠና ረጅም ጥናት እንዲያደርጉ ማስገደድ አይገባም።

አዲስ ኪዳንን ለማስተማር የምንከተላቸው መመሪያዎች በሁለት መጻሕፍት ይዘት፥ ዓላማ፥ ስልትና መጠን ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በምዕራፍ ዐሥር ላይ የዮሐንስን ወንጌል ለረጅም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ፥ በምዕራፍ ዐሥራ አንድ ላይ ደግሞ አንደኛ ተሰሎንቄን አጫጭር ለሆኑ መጻሕፍት የማስተማሪያ ምሳሌ እናደርገዋለን። በሁለቱም አካሄዶች የምንከተለው መንገድ፥ የአዲስ ኪዳንን መሠረታዊ ትርጉም በማብራራትና፥ ለዛሬዎቹ ክርስቲያኖች የሚሰጠውን ጥቅም በማመልከቱ ላይ ነው።

# ፫

## ብሉይ ኪዳንን ማብራራት (1)

### የአንድ መጽሐፍ ክፍሎች

ለዚህ ሥራችን እንደምሳሌ የምንጠቀምበት ከብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት መካከል አንዱ የሆነውን መጽሐፈ መሳፍንትን ነው:: ይህን መጽሐፍ በሳምንት አንድ ምዕራፍ አዘጋጅቶ በመስበክ ለሃያ አንድ ሳምንታት በምናደርገው ስብከት እንጨርሰዋለን ብለን ተስፋ ማድረግ የለብንም፤ ይህን የመሰለ ዝግጅት ሊታሰብም አይገባም:: በሌላ በኩል መጽሐፉን በሙሉ በሁለት ወይም በሦስት ስብከት ለመሸፈን ብንወስን ውጤታችን መጽሐፉን መዳሰስና ማንበብ ብቻ ይሆናል:: ስለዚህ ማድረግ የሚኖርብን፥ ቤተ ክርስቲያን እንድንናገርበት የምትመድብልንን ፕሮግራም ተቀብለን፥ በዚያ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ በመጽሐፉ ላይ ጥናትና ዝግጅት ማድረግ ነው:: የተመደበልን ሁለት ወይም ሦስት ክፍለ ጊዜ ቢሆን፥ ብዙ ክፍሎችን ለማካተት እንሞክር፤ በዚያ ፈንታ በመጽሐፉ ላይ አጠቃላይ ቅኝት በማድረግ በተረፈው ጊዜ በተመረጡ ሁለት ወሳኝ ክፍሎች ወይም ዐውደ ሐሳቦች ላይ ብንነጋገር የተሻለ ይሆናል::

ይህን የአዘገጃጀት ምሳሌ በመከተል፥ በዚህ መጽሐፍ ላይ ·ስድስት የግማሽ ሰዓት ስብከቶችን እናደርጋለን እንበል:: ይህ ዝግጅት የመጽሐፉን አብዛኛ ውን ክፍል በአጥጋቢ ሁኔታ ለማዳረስ በቂ ነው:: መጽሐፉን በተቻለ መጠን የመከፈያ ስፍራውን እየጠበቅን በስድስት እንከፍለዋለን:: ስድስቱን ክፍሎችም ከምዕራፍ 1-3 (መግቢያና ከመጽሐፉ ጥቂቱ ክፍል)፥ ከምዕራፍ 4-5 (ዲቦራ)፥ ከምዕራፍ 6-9 (ጌዴዎንና አቤሜሌክ)፥ ከምዕራፍ 10-12 (ዮፍታሔ)፥ ከምዕራፍ 13-16 (ሶምሶን)፥ ከምዕራፍ 17-21 (ነገዶቹን በተመለከተ) መመደብ ይቻላል::

መጽሐፍን ከፋፍሎ የመመልከት ሁኔታ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ላይ የሚገኙትን ታሪኮች እናብራራለን ሳይሆን ለምናጠናቸውና ለምናብራራቸው ታሪኮች ድንበር ሆኖ ያገለግለናል ለማለት ነው:: ለምሳሌ መጀመሪያ በምንናገርበት ርእስ ጉዳይ ላይ፥ ከምዕራፍ 1-3 ባሉት ክፍሎች ጥናት አድርጎ ዝግጅት ለማድረግ ጊዜ አይበቃንም ብለን እናስብ ይሆናል፤ ይህ ከሆነ ስለ ጎቶንያልና ስለ ናዖድ የሚናገሩትን ክፍሎች ልናስቀር እንችላለን:: ይህን ማድረጋችን የሁለቱን መሳፍንት ታሪክ በመናቅ ሳይሆን ባለን አጭር ጊዜ በሌሎች ተስማሚ መረጃና ሐሳብ ላይ በማተኮር ከእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ወስዶ ለማለፍ ተብሎ ነው::

በአሁኑ የጥናትና የዝግጅት ጊዜያችን ደግሞ እንደ ምሳሌ አድርገን የምንጠቀምበት ከዚህ በላይ ከገለጽናቸው ስድስት ክፍሎች ውስጥ ከምዕራፍ 6-9

የተጠቀሰውን ነው:: ይህ ክፍል ከምዕራፍ 6-8 ስለ ጌዴዎን ታሪክ፥ በምዕራፍ 9 የልጁን፥ የአቤሜሌክን ታሪክ ይዟል:: በእነዚህ አራት ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ስፍራዎች፥ ሰዎች፥ እንቅስቃሴዎችና ድርጊቶች ስለ ተጠቀሱ በግማሽ ሰዓት ውስጥ እነዚህን ሁሉ በዝርዝር እንናገራለን ብለን ብንነሣ አድማጮቻችንን ግራ እናጋባለን:: እንዲህ ባለው የጊዜ ጥበት ላይ የአቤሜሌክን ታሪክ በሙሉ ትተን የጌዴዎንን ታሪክ ለማቅረብ እንገደዳለን::

(እነዚህና ሌሎችም የጥናትና ዝግጅት ምሳሌዎች በሚቀርቡበት ጊዜ፥ አድማጮች ገላጭ የሆኑ አስተያየቶችን ለመከታተልና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገኙ ነጥቦችን እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውሉ መገንዘብ እንዲችሉ የሚፈለጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ከፍተው መገኘት አለባቸው)::

**ጌዴዎንን ለማስተዋወቅ**

መሳፍንትን በተመለከተ ያቀረብነው ዝግጅት ተደጋጋሚነት ያለውን የእስራኤልን ታሪካዊ ገጽታ አስቃኝቶናል:: እንደ ገና የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ስለ መራቃቸው፥ የከነዓናውያንን አምልኮ ጣዖት ስለ መከተላቸው፥ በጎረቤት አገሮች ሕዝቦች ተፅዕኖ ሥር ስለ መውደቃቸው፥ በዚህ ዐይነት ሕይወትና በጭቈና ከኖሩ በኋላ ምሕረትን ለማግኘት ወደ እግዚአብሐረ ስለ መጮኻቸው፥ ከዚህ ጩኸታቸውም የተነሣ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን አባሮ ነጻነትን የሚሰጣቸው መሪ እንደ ላከላቸው አጭር ዳሰሳ እናደርጋለን:: እነዚህ ከጠላቶቻቸው እጅ የሚቤዧቸው መሪዎች ለሕዝቡ ሲፈርዱና ጠላቶቻቸውን ድል ሲያደርጉ፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያውጁ ስለ ነበር መሳፍንት ተብለው ተጠሩ::

ምክንያቱም በመሳፍንት ውስጥ የተመዘገቡት ታሪኮች አብዛኛውን ጊዜ የሚገልጹት በእስራኤል ሕዝብ ውስጥ ስላሉ ጐሳዎችና አካባቢዎች ነው:: ስለሆነም ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችንን በምንቀጥልበት ጊዜ ግልጽ የሆነ ካርታ ቢኖረን አድማጮቻችንን የበለጠ ሊረዳቸው ይችላል::

ይህን የታሪክ ጥናታችንን ከምዕራፍ 6 ውስጥ የመጀመሪያዎቹን አራት ጥቅሶች በማንበብ እንቀጥላለን:: ሆኖም፥ ጥቅሶቹን ቆም ሳንል በቀጥታ ማንበብ የለብንም፤ እንዲሁም የእያንዳንዱን ጥቅስ ቃልም አናነብም:: ለዚህ አካሄድ ጠቃሚ የሚሆነው ክፍሎቹን ስናነብና ስናብራራ ሳለን አድማጮቻችን ሊከታተሉን እንዲችሉ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ከፍተው እንዲገኙ ማበረታታት ነው:: ቍጥር 1ን ስናነብ በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ጨቋኞች ምድያማውያን መሆናቸውን፥ የእነዚህ ሰዎች የጭቈና ጊዜም ለሰባት ዓመታት የዘለቀ መሆኑን ማስተዋል አለብን:: በተጨማሪም እነዚህ ምድያማውያን የመጡት ከእስራኤል ደቡብ ክፍል ተነሥተው ወደ ሰሜን በመንቀሳቀስ የሙት ባሕርን ዙሪያ ካጠቁ በኋላ እየገፉ

መጥተው በምሥራቅ አቅጣጫ ወደ እስራኤል የገቡ መሆናቸውን እንገልጻለን:: ካርታችን ምድያማውያን የተጓዙበትን መስመር ሊያመለክተን ይችላል::

ቁጥር 2-3 በምናነብበት ጊዜ ምድያማውያን ምን ያህል እስራኤላውያንን ይጨቁኑና ያሰቃዩ እንደ ነበሩ መገንዘብ እንችላለን:: የእስራኤላውያንን ምድር በቋሚነት አልያዙም፤ ነገር ግን በየዓመቱ የእስራኤላውያንን እርሻ ይወርሩ ነበር:: ቀጥለን በቁጥር 4 ላይ በምናነብበት ጊዜ፥ ይህ ወረራ ከደቡብ እስራኤል ጀምሮ በጋዛ አድርጎ እስከ ሜድትራንያን ባሕር ዳርቻ ድረስ ይዘልቅ ነበር፤ በኋላም ንፍታሌም ሰሜናዊ ክፍል ተስፋፍተው እናገኛቸዋለን:: ስለ ንፍታሌም የሚናገሩትን ጥቅሶች በኋላ ስለምናገኛቸው፥ አሁን መመልከት አያስፈልገንም:: እነዚህን ቦታዎች በካርታችን ላይ ማግኘት ይኖርብናል፤ ወረራ የተካሄደባቸውን ስፈራዎችም ምልክት እናደርግባቸዋለን:: ምድያማውያን ወረራውን ለማካሄድ የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር ነበረባቸው:: ይህ ኋላ የሚጠቅም ጥቂት መረጃ ነው::

እስከዚህ ድረስ አራት ጥቅሶችን ብቻ አነበብን፤ ይሁን እንጂ ሰዎች በቁጥር 5 ላይ ስለ ግመሎች የተጠቀሰውን ልብ እንዲሉ ልናስታውሳቸው ይገባል:: ጥቅሱን ልናነብላቸው አያስፈልግም፤ በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ እንደ ገና በመመልከት «ግመሎች» የሚለውን ቃል እንዲያገኙ እንነግራቸዋለን:: ይህ ታሪኩን ከገሃዱ ዓለም ጋር ትሥስር እንዲኖረው የሚያደርግ ማብራሪያ ነው::

ጌዴዎን የተባለው ሰው የእስራኤልን ጠላቶች እንዲያባርርላቸው እግዚአብሔር የተጠቀመበት ነው:: የዚህን ሰው ጉሳና ነገድ በማብራራት ለአድማጮቻችን ማስተዋወቅ እንችላለን:: የዚህ ነገድ ተወላጆች በእስራኤል ሰሜናዊ ክፍል በሚገኝ በምናሴ መሬት ላይ ይኖሩ ነበር፤ በምድያማውያን ወረራና ጭቈና ይሰቃዩ ከነበሩት ነገዶች መካከል ነበሩ:: ይህን ሁሉ በቁጥር 11 ላይ እንመለከታለን:: «ምናሴ» የሚለውን ቃል እስከ ቁጥር 15 አናገኘውም፤ ሆኖም ይህ ሊያስጨንቀን አይገባም፤ አንባቢዎቹ ቁጥር 15 ስንደርስ ያገኙታል)::

የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍል ለማብራራት ልዩ ልዩ አማራጭ መንገዶች እንዳሉ ልብ እንበል:: በዚህ ሁኔታ ለአድማጮቻችን የጥቅሱን ክፍል ሳናነብላቸው ማብራሪያውን አሰምተናቸዋል ማለት ነው፤ «ቁጥር 11ን ብተመለከቱ ይህን ትረዳላችሁ» በማለት መረጃውን ብቻ እንሰጣቸዋለን:: አብዛኛዎቹ ሰዎች ቁጥር 11ን እንዲመለከቱ የነገርናቸውን በቀጥታ ሳይሰሙ ይፈጽማሉ:: ነገሩን በግልጽ ሳይሆን በዘዴ፥ ይህን ሐሳብ ለመረዳት ሌላ ከፍ ያለ ትምህርት እንደማያስፈልግ፥ ለማለት የሚገባውን ነጥብ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኝ ልንነግራቸው እንችላለን:: እኛ የምናደርገው ለማለት የሚገባውን ፍሬ ነገር ራሳቸው እንዲደርሱበት ስሜታቸውን መቀስቀስ ነው:: በዚህም መጽሐፍ ቅዱስን እንዲመለከቱ ፍላጎት ካሳደርንባቸው አንድ ትልቅ ሥራ ሠራን ማለት ነው::

ጌዴዎን ምድያማውያንን አባሮ የእስራኤልን ሕዝብ ነጻ እንዲያወጣ እግዚአብሔር ሊጠቀምበት እንደ መረጠው ባወቀ ጊዜ በጣም ፈራ፣ ተጠራጠረም፣ ግን እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋና ኀይል ተረጋጋ:: ከቍጥር 14-16 ባለው ክፍል ላይ እንደምናነበው ፍሬ ነገሩ ለአድማጮቻችን ሕይወት የሚጠቅም መሆኑን እንረዳለን:: ከእኛ አብዛኞቻችን ልክ እንደ ጌዴዎን ፈሪዎችና ተጠራጣሪዎች ነን፣ ይሁን እንጂ እኛ ለእግዚአብሔር ጠቃሚዎች የመሆናችን ጉዳይ በእግዚአብሔር ላይ ያለ የእኛ ዝግጁነት ነው እንጂ በማንነታችን ወይም በችሎታችን ላይ የተመሠረተ አይደለም:: ይህን ነጥብ ጥቂት ማብራራት ቢኖርብንም ብዙ ልንቆይበት አይገባም፣ ጠቃሚው ነገር ከጥቅሱ መልእክት ውስጥ ለሕይወታችን የሚበጀውንና በተግባርም ላይ የምናውለውን ነጥብ ነቅሰን በመጠቀሙ ላይ ነው:: እግዚአብሔር በቍጥር 21 ላይ በገለጠው ተአምራዊ ምልክት ሳቢያ ስላደረገው ማረጋገጫ በመግለጽ ይህን ክፍል ልንደመድም እንችላለን::

## ጌዴዎን ሥራውን ጀመረ

ጌዴዎን እንዲረጋጋና ተግባሩን እንዲጀምር እግዚአብሔር ካረጋገጠለት በኋላ ወዲያውኑ ሥራውን ጀመረ:: ዛሬም የእግዚአብሔር ሕዝብ ይህንኑ ፈለግ መከተል ይኖርበታል:: የጌታ እናት ማርያም በቃና ዘገሊላ÷ በሠርግ ቤት በነበረችበት ጊዜ «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» (ዮሐ. 2÷5) ብላ ለአገልጋዮች የነገራቸቸውን ቃል ማስታወስ ይገባናል:: ጌዴዎንም አገልግሎቱን የጀመረው አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ÷ ያውም በጣም አስቸጋሪ በሆነ ስፍራ÷ በራሱ አገር ነው::

የእስራኤል መከራ የመጣው ከጣዖት አምልኳቸው የተነሣ ስለ ሆነ የጌዴዎን የመጀመሪያው ተግባር ሕዝቡ የጣዖት አምልኮን ጨርሶ ትቶ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ማድረግ ነበር:: የራሱ አባት በኣል ለተባለው ጣዖት መሠውያ ሠርቶ ይሰግድለት ስለ ነበር÷ ይህ ለጌዴዎን አስቸጋሪ ነበር:: ቢሆንም÷ ጌዴዎን እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ ለማድረግ ቈርጦ ተነሣ:: የበኣልን መሠውያ እንዴት ሰባብሮ እንደጣለና ለእግዚአብሔር መሠውያ ሠርቶ መሥዋዕት እንዳቀረበ ከ6÷25-27 ድረስ እናነባለን:: ጌዴዎን የሚደርስበትን ተቃውሞ በመፍራት የማፈራረሱን ተግባር የፈጸመው በሌሊት ነበር:: ታዲያ ይህን በማድረጉ ልንተቸው አይገባም:: ቢያንስ እግዚአብሔር ያዘዘውን በሚመቸው መንገድ ፈጽሟል፣ እኛም እግዚአብሔር የሚያዝዘንን መፈጸም ይጠበቅብናል:: የምንፈጽመውን ተግባር በጀግንነት ወይም በፈሪነት መንፈስ ብንፈጽመው ይህ ከግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም፣ ዋናው ነገር ታዛዥነታችን ነው::

ከዚያም ወደ 6÷28 እናመራና የከተማው ሰዎች ጌዴዎንን ለመግደል እንዴት እንደተነሡ አድማጮቻችን እንዲከታተሉ እናደርጋለን:: የእግዚአብሔር ሰዎች እርሱ የማይወዳቸውን ተግባራት ለማስወገድ ሲነሡ ተቃውሞ መነሣቱ

የሚጠበቅ ነው፤ ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ ካልጠበቅነው ምንጭ ድጋፍ እናገኛለን:: ለምሳሌ :- የበኣል መሠውያው የተሰባበረበት የጌዴዎን አባት በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ተመለሰ፤ የከተማው ሰዎች ጌዴዎንን እንዳይጎዱትም ከጎኑ ቆመ፤ (6÷31ን ይመ.):: ጌዴዎን ተግባሩን በመቀጠል ሠራዊት ለማቋቋም ሕዝቡን በጠራ ጊዜ ሊገድሉት ይፈልጉ የነበሩት አቢዔዝራውያን በሠራዊቱ ውስጥ በፈቃዳቸው ለመመልመል የመጀመሪያዎቹ ነበሩ:: ከቍጥር 33-35 ያለውን ስንናብ የአቢዔዝራውያን ተሳትፎ ምን እንደ ነበረና ሌሎችን ዝርዝር ነጥቦች እናገኛለን::

ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡበት ጊዜ ታዋቂ ያልሆኑ ሰዎችን÷ ስሞችንና ቦታዎችን ግምት ሳይሰጧቸው ያልፏቸዋል፤ እነዚህን ጥቅሶች በምናነብበት ጊዜ ግን እንዲህ ያሉት ሰዎች ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ለማጤን ዕድል ይቸሩናል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝር ትምህርታችንን ከካርታ ምልከታ ጋር በማያያዝ ምድያምውያን እንዴት ከምሥራቅ በመነሣት የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው በእስራኤል ሰሜን በኢይዝራኤል ሸለቆ እንደ ሠፈሩ ማሳየት እንችላለን:: ይህ የኢይዝራኤልን ሸለቆ የምናሴን (የጌዴዎንን ጐሳ)÷ የአካባቢውን አጐራባች ምድር በስፋት እንደሚሸፍን መገንዘብ አለብን:: የጌዴዎን ሠራዊት የተመለመለው ከእነዚህ ከሰሜን ነገዶች ነበር፤ ይህ በሚከተለው የጦር ሜዳ የተረጋገጠ ነው::

ከምድያምውያን ጋር የሚደረገው ግጭት ተፋፍሞ ምድያማውያን እየቀረቡ ሲመጡ ሳሉ የጌዴዎን እምነት ደከመ:: ስለዚህ ጌዴዎን ሌላ ማረጋገጫ የሚሆንለትን ተአምር እግዚአብሔር እንዲያሳየው ጠየቀ:: ጌዴዎን ሌላ ተአምር መጠየቅ አልነበረበትም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ ድል ታደርጋለህ ብሎ አረጋግጦለት ነበር:: ስለዚህ ጌዴዎን እምኖ ብቻ መታዘዝ ነበረበት:: እግዚአብሔር ግን በጸጋው ብዛት ጌዴዎን የጠየቀውን ምልክት አሳየው::

ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ክፍል ደጋግ አድርገው ስለሚያውቁት ምናልባት ቆም ብለን ማንበብ ላያስፈልገን ይችላል:: እዚህ ላይ መጥቀስ የሚገባን ምንም እንኳን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ልዩ ምልክት እንዲያሳያቸው መጠየቅ እንዳለባቸው ባናበረታታም በአኳያው ልዩ ምልክት የሚቀበሉትን ደግሞ መንቀፍ የለብንም:: እግዚአብሔር ሉዐላዊ አምላክ ስለ ሆነ የመረጠውን ሊያደርግ ይችላል:: ማናችንም ብንሆን ፍጹማን አይደለንም፤ ሆኖም ግን እግዚአብሔር በጸጋውና በፍቅሩ ብዛት ከእኛ ጋር ግንኙነትን ያደርጋል፤ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ይህን በዚህ መንገድ እንደሚያደርግ እንገነዘባለን::

## ከምድያማውያን ጋር የተደረገ ጦርነት

እስራኤላውያን የድላቸው ምንጭ የራሳቸው ኀይል ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን እንዲያውቁ÷ ጌዴዎንም ለጦርነት የሚያስልፋቸው ሰዎች ብዛት ሦስት

መቶ ብቻ እንዲሆኑ አዘዘው:: ይህንን ሁኔታ ምዕራፍ 7÷23 በማንበብ አንድ ነገር ሠርተን ሲሳካልን÷ ይህ ውጤት ሊገኝ የቻለው ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከራሳችን ችሎታ የተነሣ መሆኑን እንድናምን ከሚያደርገን አጉል ዝንባሌያችን ጋር ልናመዛዝነው እንችላለን:: በዚሁ ነጥብ ላይ ትምህርት የሚሰጡንን ክፍሎች ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍ÷ ለምሳሌ እንደ 2ቆር. 4÷7 ፤ 12÷9 እና ፊል. 3÷7-11 ያሉትን መመልከት እንችላለን:: ለጦርነት ተብለው የተጠሩ ሰዎች ወደ ወንዝ ሄደው በምን አኳኋን ውሃ እንደጠጡ በዝርዝር መወያየቱ አስፈላጊ አይሆንም:: ዋናው ቁም ነገር እግዚአብሔር በውሃ አጠጣጥ አኳኋን ለጦርነት የተጠሩት ሰዎች እንዲቀንሱ የማድረጉ ጉዳይ ነው::

በምድያማውያን ላይ ስለወረደው ድንገተኛ ፍርሃት የሚናገረውን ከቍጥር 13-14 ያለውን ክፍል አድማጮቻችን እንዲያጤኑ ልናነብላቸው እንችላለን:: ከምድያማውያን ወታደሮች ውስጥ አንዱ «በሕልሜ ክብ የሆነ አንድ የገብስ ቂጣ ከላይ ተንከባሎ በምድያማውያን ሰፈር ላይ ሲወርድ÷ ድንኳኑንም ሲመታው÷ ካመታቱም ኀይለኛነት የተነሣ ድንኳኑ ተገልብጦ ሲፈርስ አየሁ፤» ሲል ለጓደኛው አጫወተው:: ጓደኛውም ሕልሙን ሲፈታ «ይህ ሌላ ሊሆን አይችልም እነዚህ ድኾች የሆኑ እስራኤላውያን የምድያማውያንን የጦር ሰፈር ወረው ያጠፉታል ማለት ነው»፤ አለ:: ቀደም ሲል ምድያማውያን የእስራኤላውያንን ሰፈር በቀላሉ ይደመስሱ ነበር:: ጌዴዎን ይህን የመሰለ ያልታሰበ ፍርሀት በምድያማውያን ዘንድ መኖሩን ሲሰማ በጦርነቱ ላይ ድልን እንደሚቀዳጅ እርግጠኛ ሆነ:: ቍጥር 15ን ስናነብ ለአድማጮች የምናሰማውን አበረታች መልእክት እናገኛለን::

እስራኤላውያን በምድያማውያን ሰፈር ላይ የጣሉት አደጋ በሚገባ ስለሚታወቅ ማንበብ አያስፈልገንም:: ነገር ግን መንፈቀ ሌሊት ላይ እስራኤላውያን ቀንደ መለከቶቻቸውን እየነፉ÷ ማሰሮቻቸውን እየሰበሩና እየጮኹ ወደ ሰፈሩ ሲገቡ ምድያማውያን ስላጋጠማቸው ፍርሀትና ድብልቅልቅ ሁኔታ ባጭሩ÷ ጠቅለል በማድረግ ልናቀርብ እንችላለን:: በመቶ የሚቈጠሩ የችቦ መብራቶችን በሠፈራቸው ዙሪያ ባዩ ጊዜ እጅግ ብዙ የእስራኤላውያን ተዋጊ ሠራዊት የመጣባቸው መሰላቸው:: ብዙዎች በጨለማው ውስጥ በአካባቢያቸው ውልብ በሚለውና በሚንቀሳቀሰው ነገር ላይ ሰይፋቸውን ይመዙ ጀመር፤ ይህን በማድረግም የራሳቸውን ሰዎች ገደሉ፤ የቀሩት ነፍሴ አውጪኝ ብለው በኢይዝራኤል ሸለቆ አድርገው የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር ሸሹ::

የምድያማውያንን የጦር ሠፈር በእኩለ ሌሊት በማጥቃቱ ተግባር ላይ የተሠማሩት ሦስት መቶ ሰዎች ብቻ ነበሩ፤ ከዚያ በኋላ ግን ብዙ የእስራኤል ሠራዊት ከሦስት መቶዎቹ ጋር ተቀላቀሉ:: ቀደም ሲል ጌዴዎን ሠራዊቱን መልምሎ በማደራጀት ረገድ ስለፈጸመው ተግባር የገለጽንበት ክፍል ቍ 23 ትልቅ ስፍራ ስለሚሰጠው ልናነበው ይገባል፤ (6÷35 ይመ.):: አንድ ጥቅስ እጅግ ጠቃሚ መስሎ በማይታይበት ጊዜ እንኳ አንብበን ስንወያይበት እጅግ የሚስብና ጠቃሚ

እንደሚሆን ማስታወስ ያስፈልጋል፤ (አስቀድመን እናንብበው፤ ከዘያም እንወያይበት)። ይህን የመሰለው ልምምድ ስብከቱን ፊሬያማ ከማድረጉም በላይ ጊዜን ይቈጥባል። እንደዚህም ከየምዕራፉ የተመረጡ ጥቅሶችን ብቻ በማንበብ፥ በተነቃቃ ሁኔታ ስብከታችንን መቀጠል እንችላለን። በተመሳሳይ ሁኔታ የምንባብ ማመሳከሪያችንን መናገርም የአድማጮቻችንን ስሜት ጠብቆ መቀጠል ያስችላል።

## የተዋጣለት ድል

ምንም እንኳ ዋናው የእስራኤል ተዋጊ ኀይል የመጣው ሰሜን ካሉት ነገዶች ቢሆንም፥ የጌዴዎን ቡድን ከመካከለኛው የእስራኤል ዋና ክፍል፥ ከኤፍሬም ነገድ የተመለመለና የዚህ ቡድን እዝ ዋና ተግባር በዮርዳኖስ ወንዝ መሻገሪያ ላይ ሆኖ የምድያውያንን የማምለጫ ቀዳዳ መዝጋት ነበር። ይህን ታሪክ ለአድማጮቻችን ከነገርን በኋላ ከቊጥር 24-25 ያለውን እያነበብን ድርጊቶቹን በካርታው ላይ እናሳያለን። ጥቅሶችንም እያነበብን የኤፍሬማውያን ሠራዊት የምድያማውያን ሠራዊት አዛዦች የነበሩትን ሁለት ልዑላን መግደላቸውን ትኩረት ሰጥተን እንናገራለን።

በምዕራፎች መካከል ባሉ መሸጋገሪያዎች ወይም መግቻ ስፍራዎች ሳናቆም (ምናልባት የዋናው ቅጅ ምራፎችና ቊጥሮች የሉትም ይሆናል)፥ ያለውን ግን ምዕራፍ 8ን ከቊጥር 1-3 እናነባለን። ከቊጥር 1 ጀምረን ስንሰብክ የኤፍሬም ወገን የሆኑት ሰዎች ጌዴዎን ወደ ዋናው ጦርነት ስላልጠራቸው እንዳጉረመረሙበት እናነባለን። በየትኛውም ዘመን በየትኛውም ሀገር ተመሳሳይ ሰዎች ያጋጥሙናል። ይህ ችግር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳ አለ። የራሳቸውን ጥቅም የሚያስቀድሙና እኛ ያልነው ብቻ ይሁን የሚሉ ሰዎች በቀላሉ ይከፋሉ። ቀናተኛ ሰዎችም ቅያሜያቸው ከአፍንጫቸው ሥር ነው። ይህን መሰል ስህተት በሌሎች ሰዎች ላይ ስለምንመለከት ብቻ ሳይሆን እኛ ራሳችን ከእነዚህ ችግሮች የነጻን አይደለንም። ይሁን እንጂ እነዚህን ነገሮች አብዛኛዎቹ ሰዎች ወዲያውኑ ሊያጤኗቸው ስለሚችሉ በትምህርቱ ላይ ሰፋ አድርጎ መወያየት ላያስፈልግ ይችላል። ዋናው ችግራችን ትክክለኛውን ነገር ከመገንዘቡ ላይ ሳይሆን ተግባራዊ ከማድረጉ ላይ ነው።

አድማጮቻችን «እንደ አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ» ባለ ቀላል አማርኛ የተተረጐመ መጽሐፍ ቅዱስ በእጃቸው ከሌለ ጌዴዎን ለኤፍሬም ሰዎች፥ «የኤፍሬም የወይን ቃርሚያ ተጠቃሎ ከገባው ከአብዔዘር የወይን መከር አይበልጥምን?» ብሎ የተናገረውን አብራርቶ መግለጽ ያሻል። የዚህ አነጋገር ሥዕላዊ አገላለጽ የወይን መከር መሰብሰብን ያመለክታል። የተሰበሰበው ምርትም መከር ተብሎ ሲጠራ ከዋናው ሰብል በኋላ የቀረው ክፍል ቃርሚያ ተብሏል። ጌዴዎን አመጣጡ ከአብዔዘር ጐሣ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ እርሱና ሠራዊቱ በዋናው

ጦር ላይ አያሌ ምድያማውያንን ደመሰሱ፤ (እነዚህ ዋናዎቹን መከሮች ሰበሰቡ)። ኤፍሬማውያን ግን የዮርዳኖስን ወንዝ ለመሻገር በመሸሽ ላይ የነበሩትን ጥቂት የምድያማውን ሠራዊት ብቻ ገደሉ፤ (ቃርሚያዎች የተባሉት እነዚህ ናቸው)።

ጌዴዎን «የለዘበች ምላስ ቍጣን ታበርዳለች» (ምሳ. 15፥1) የሚለውን የጥበብ ቃል በማስታወስ የኤፍሬም ሰዎች ካገኙት ቃርሚያ ጋር የእርሱ ዋና መከር ሲመዛዘን ከምንም የማይገባ መሆኑን በጥበብ ተናግሮ አረጋጋቸው። ጌዴዎን በጦሩ ሜዳ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ምድያማውያንን የሚፈጅ ታላቅ ጦር ይመራ ነበር፤ (ቍጥራቸውን በተመለከተ 8፥10 ይመ.)። ነገር ግን እነዚህ፥ እርሱ የፈጃቸው፥ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ተዋጊዎች፥ ተራ ጦረኞች ነበሩ። የኤፍሬም ወገን ሠራዊትም ቢሆኑ የፈጁት ጥቂት በሺህ የሚቈጠሩ ወታደሮችን ነበር፤ በመሀላቸው ግን ሁለት ዋና የጦር ጀኔራሎች ነበሩ። ጌዴዎን «እስቲ ልጠይቃችሁ እናንተ ካደረጋችሁት ጋር ሲነጻጸር የእኔ ከምን ይቈጠራል?» አላቸው። የኤፍሬም ሰዎች ይህን ከንቱ ሙገሳ ወደዱት፤ መጽሐፍ ቅዱስም ቀጥሎ ስለዚህ ሁኔታ ሲናገር «ይህንን ሲሰሙ ቍጣቸው በረደ»፤ ይላል። ሲያስቡት ያሳዝናል። ብዙ ጊዜ ከሰዎች ኩራትና ትዕቢት ጋር የሚስማማ ሁሉ በእነርሱ ዘንድ ተቀባይነት አለው። እኛም ራሳችን ብንሆን የሚያሞጋግሱን ሰዎች በሚያጋጥሙን ጊዜ ውስጣችን በደስታ ይረካል።

## የስኬት አደጋዎች

የምድያማውያን ሽንፈት ታሪክ በዚህ ያበቃል ብለን እናስብ ይሆናል። ታሪኩ እንዲህ ቢሆን ኖሮ ጥቂት ስህተቶች ብቻ እንደ ነበረው የተነገረለት ጌዴዎን የእምነት ሰው ሆኖ በቀረ ነበር፤ (ዕብ. 11፥32 ይመ.)። መጽሐፍ ቅዱስ የመዘገባቸው፥ ጀግኖች በሁሉም ነገር ፍጹማን አልነበሩም። የጌዴዎን ታሪክ በኋላ እንደሚያስረዳው ይህ ሰው ቀድሞ የነበረውን በእግዚአብሔር ላይ የመደገፍ ባሕርይ ትቶ፥ በኀይሉና በስኬቱ የመመካት አደጋ ውስጥ የመውደቁ ሁኔታ፥ ኀይልና ስኬት እንዲህ ያለ የከፋ ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያ ሊሆኑን ይችላሉ።

ለስብከት የተመደበልን ሰዓት ስለማይበቃን በዚህ በኋለኛው ክፍል ላይ ብዙ መነጋገር አንችልም። ሆኖም የታሪኩን ቅደም ተከተል ዋና ዋናውን ነጥብ ለአድማጮቻችን መናገር እንችላለን። የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው የሸሹት ምድያማውያን አሁን ከእስራኤል ምድር ውጪ ስለ ነበሩ ጦርነቱ ያበቃ መስሎአቸው ይሆናል። ነገር ግን ጌዴዎን ሁለቱ የምድያም ነገሥታት ወንድሞቹን በጦርነት ላይ ስለ ገደሉበት ሊበቀላቸው ቈረጠ። ከዮርዳኖስ ምሥራቅ የሚገኙ የሁለቱ የእስራኤላውያን ከተሞች መሪዎች ጌዴዎንን በዚህ ጦርነት ላይ ሊተባበሩት አልፈለጉም። ይህን ያደረጉበት ምክንያትም የምድያማውያን ሠራዊት ተመልሰው መጥተው ይገሉናል በሚል ፍርሀት ነበር። ጌዴዎን ግን ያለ እነርሱ ርዳታ ወደ ፊት ቀጠለና ሁለቱን የምድያም ነገሥታት ከማረከ በኋላ ተመልሶ

ቀደም ሲል ለዚህ ጦርነት ያልተባበሩትን እነዚያን የእስራኤል ከተሞች ሰዎች ቀጣ፤ ሁለቱን ነገሥታትም ገደለ፡፡

ጌዴዎን እነዚህን ተግባራት የፈጸመው ልክ በዙሪያው እንዳሉ ነገሥታት ሆኖ ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ ድርጊት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ እናንግሥህ ቢሉት የሚያስገርም አልነበረም፡፡ በዚህ አጋጣሚ ምዕራፍ 8፥22 ከቍጥር 23 ጋር አጣምረን ስናነብ ጌዴዎን ለሠራው ወሮታ ሕዝቡ በላያችን ላይ ንገሥ ብለው በለመኑት ጊዜ ልመናቸውን አልተቀበለም፡፡

ይሁን እንጂ ጌዴዎን በምድያማውያን ጦርነት ጊዜ በነበረው ሁኔታ፥ በሰላሙ ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ አልሆነም፡፡ ልክ አንድ ጊዜ አሮን እንዳደረገው ሁሉ፥ በማይታየው አምላክ ፈንታ የሚታይ ምልክትን ተካ፡፡ ይህ እርሱ የተካው ነገር በኋላ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ጣዖት ሆኖ ተቈጠረ፤ (ቍጥር 27 ይመ.)፡፡ ጌዴዎን ምንም እንኳን የንጉሥ ማዕረግ አግኝቶ በአዋጅ ባይነግሥም የኖረው ልክ እንደ ንጉሥ ነበር፡፡ በዚህም ብዙ ሚስቶች፥ ብዙ ዕቁባቶችና በርካታ ልጆች ነበሩት፡፡ ከልጆቹ መካከል አንዱ አቤሜሌክ ይባል ነበር፤ የስሙ ትርጉምም «አባቴ ንጉሥ ነው» ማለት ነው፤ (ከቍጥር 29-31 ይመ.)፡፡

ስብከታችንን በአሉታ ሐሳብ መደምደም አንፈቅድም ይሆናል፤ ዳሩ ግን የጌዴዎን ታሪክ የሚደመደመው በዚህ መንፈስ ነው፡፡ ሥልጣንንና ስኬትን አመዛዝኖ መያዝ አስቸጋሪ እንደሆነና የኋላ የኋላ የመንፈሳዊ ሰውን ሕይወት ሊያበላሽ እንደሚችል ታሪኩ ያመለክታል፡፡ ጌዴዎን በአንድ ወቅት እስራኤላውያንን ከምድያማውያን ጭቈና ነጻ ሊያወጣ በሚያስችለው ሁኔታ ለእግዚአብሔር ታዛዥ ሆኖ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ መንፈሱ ጸንቶ እስከመጨረሻው አልኖረም፡፡ እኛም ብንሆን እንዲሁ ነን፡፡ ክርስትና ቀን በቀን ከእግዚአብሔር ጋር እንድንራመድ የሚፈልግ ሕይወት ነው፡፡ ምናልባትም እንደ ጌዴዎን ወይም እንደ ሌሎች መሳፍንት የታወቅን የእምነት ሰዎች ልንሆን እንችላለን፤ ዋናው ቁም ነገር ግን ይህን እምነት እስከ መጨረሻው ይዘን መዝለቅ መቻላችን ነው፡፡

## ተጨማሪ አስተያየቶች

ከዚህ በላይ በተመለከትናቸው የአሠራር ምሳሌዎች ለስብከት የያዝነው ማስታወሻ ወይም አርእስተ ነገር በመጀመሪያ ከሠላሳ ደቂቃ በላይ ሊወስድ የሚችል መስሎ ሊታየን ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው በሦስት ምዕራፎች ውስጥ ያሉ ፍሬ ነገሮችን በሙሉ ስናጠናና በአኗያውም በዝግጅታችን ውስጥ እንዴት አድርገን ልናካትታቸው እንደምንችል እናስብ ስለ ነበር ነው፡፡ እነዚህን ክፍሎች በስብከታችን ውስጥ አካተን ብንሰብካቸው ኖሮ ግን፥ በሠላሳ ደቂቃ ውስጥ በሚገባ በተጠቀምንባቸው ነበር፡፡

**ጌዴዎን- መሳፍንት ከምዕራፍ 6-8**

**ጌዴዎንን ማስተዋወቅ (6፥1-24)** 0
የመደጋገም ሁኔታ - የመሳፍንት ትርጉም

1-4 ምድያማያዊ - መንገዱ - ዓመታዊ ወረራ - ጋዛ፣ ንፍታሌም
11 ጌዴዎን ከምናሴ፥ አብኤዘር - ፍርሀትና መጠራጠር
14-16 እግዚአብሔር ጌዴዎንን አበረታታው- ቁ 14ና16 ፥ (21 አስታውሱ)

**ጌዴዎን ተግባሩን ይጀምራል (6፥25-40)** 6

25-27 ወዲያውኑ መጀመር (ከዮሐ 2፥5 ጋር ማነጻጸር) - በቤት እጅግ አስቸጋሪ
የመጀመሪያ ደረጃ: - የሐሰት መሠውያውን ማስወገድ- የበኣልን ምንነት ማጤን
ቀጣዩ ደረጃ: - እውነተኛ መሠውያ መሥራት - መፍራት፥ ግን መታዘዝ - ከእኛ ጋር ማመዛዘን
28: የአቢዔዝራውያን ቊጣ - ጌዴዎን የሕዝቡን እምነት መቃወሙ - ተቃውሞ
31: ካላሰበው ሰው ድጋፍ ማግኘቱ - በመጀመሪያ ከተሰወጠው ከአባቱ
33-35 አቢዔዝራውያን ጌዴዎንን ተባበሩት - ምሥራቅ፣ ዮርዳኖስ፥ ኢይዝራኤል፣ የሰሜን ነገዶች የሚሉትን ልብ በሉ፤ የጌዴዎን እምነት ደከመ - ምልክቶች - ቸር እግዚአብሔር - ከእኛ ጋር ማመዛዘን

**ከምድያማውያን ጋር የተደረገ ጦርነት (7፥1-23)** 15

2 ለመጀመሪያው ጦርነት 300 ጦረኞች ብቻ - መጠጣቸውን ልብ በሉ - የእግዚአብሔር ኀይል ፥ የእኛ አይደለም- 2 ቆሮ. 4፥7 ፤ 12፥9፤ ፊል. 3፥7-11
13:14 በምድያማውያን ሰፈር ፍርሀት መነዛቱ - ስለ ሕልም ማውራት
15 ጌዴዎን ተበረታታ - ሰገደ - ከዚያም ወደ ተግባር ገባ - የጦርነቱ ሁኔታ - ምድያማውያን ፈሩ - ወደ ዮርዳኖ ሸሹ
23 ትልቁ የእስራኤል ሠራዊት አሁን ተባበረ (6፥35 ይመ.)

**የተቀጣለት ድል (7:24-8፥3)** 20

24-25 ኤፍሬም - ዮርዳኖስን መሻገር ፥ የሁለት ምድያማውያን መገደል 8፥1-3
8፥1-3 ኤፍሬም ተቀየመ - ራሱን ወዳድ - ቀናተኛ - እኛም ያው ነን?
«ቃርሚያዎች» - ዋናው መከር (8፥10) ምሳሌ : - 15፥1 ይመ.)
- ሙገሳ - ለራስ ጥቅም - ለራስ ከንቱነት

**የስኬት አደጋ (8፥4-35)** 25

እምነት (ዕብ. 11፥32) - ሁልጊዜ ግን አይደሏም - ከራስ ጋር ማስተያየት ጌዴዎን የምድያማውያንን ነገሥታት ማሳደዱ - መበቀል- የእስራኤል ከተሞች
22-23 ጌዴዎን እንደ ንጉሥ ይገዛ ነበር - ሕዝቡ ፈለጉት - እርሱ እምቢ አለ
27 ለማይታየው አምላክ ምልክት አደረጉ - ጣዖት
29:31 እንደ ንጉሥ ኖረ - ዕቁባቶች - ልጆች - «አቤሜሌክ» የአሉታው ማስታወሻ አበቃ? -የስኬትና የሥልጣን አደጋ: - ባለፈው ተሞክሮ አለመኖር - እስከ መጨረሻ መጽናት

እኛ ለአድማጮቻችን የምናነባቸው ጥቅሶች ብዛት ሠላሳ ሁለት ናቸው:: ምዕራፍ 6÷1-4 ÷ 11 ÷ 14-16 ÷ 25-28 ÷ 31 ÷ 33-35÷ ምዕራፍ 7÷2 ÷ 13-15 ÷ 23-25 ÷ ምዕራፍ 8÷1-3 ÷ 22-23 ÷ 27 ÷ 29-31:: በምንሰብክበት ጊዜ እነዚህን ጥቅሶች በቀላሉ ማየት እንድንችል በጎናቸው መስመር ማድረግ እንችላለን:: በመስበኪያው መድረክ ላይ የምናቀርበው ማስታወሻ ውስጥ ያሉ የጥቅስ ቁጥሮችም ከእነዚህ ምልክቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆን አለባቸው:: ይህን ስናደርግ ዓይናችን ከማስታወሻችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በሚመለከትበት ጊዜ ጥቅሶቹን በቀላሉ ሊያይ ይችላል::

በዝግጅታችን ጊዜ ደግመን ደጋግመን ስናነብና ስናጠና የሚወስድብንን ጊዜ እስከ መረጥነው ስፍራ ድረስ የሚኖረውን ደቂቃ በማስታወሻችን ውስጥ እንጽፋለን:: ይህን የጊዜ ተመንም በማስታወሻችን የቀኝ ጎን እንመዘግባለን:: ይህን ስናደርግ እያንዳንዱን ክፍል በምን ጊዜ መጀመር እንዳለብን ልናውቅ እንችላለን:: ስብከታችንን በተመደበልን ጊዜ ውስጥ እንድንፈጽም ራሳችንን እናሠለጥናለን

በገጽ 81 ላይ የቀረበው የምስባክ ማስታወሻ መለማመጃ በምዕራፍ 8 ላይ ያለውን ስብከት ያጠቃልለዋል:: አንድ ጊዜ በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ካሉ ተፈላጊ ምዕራፎች ጋር ከተዋወቅን፣ በሥራ ላይ ለማዋል የምንፈልጋቸውን ነጥቦች በስብከት ላይ እያለን እነዚህ ማስታወሻዎች ትዝ ይሉናል::

ምንም እንኳን ለስብከት የተዘጋጁ መልመጃዎች አንዳንድ ሁኔታዎችን ቢያመለክቱም÷ ለሞዴልነት ተብለው የቀረቡ አይደሉም:: ተግባራቸው ብዙ ገጽ የሆነ የስብከቶች ይዘቶች እንዴት በአንድ ገጽ ላይ አጥረው ለአዕምሮ ማስታወሻነት እንደሚዘጋጁ ለማሳየት ነው:: ለምሳሌ አምስቱ ዋና ርእሶች ለአድማጮች እንዲነገሩ የቀረቡ አይደሉም:: እነርሱ ስብከታችንን በምናቀርብበት ጊዜ የደረስንበትን እንዲጠቁሙን የተደረጉ ናቸው:: ስለ ርእሶቻችን ለአድማጮች ለመንገር ከፈለግን ከያዝነው ማስታወሻ ውጪ ለየት ያሉ መሆን አለባቸው:: ይህን ማድረግ የራሳችን ፍላጎት ሲሆን በጥድፊያ ስብከቱን መወጣት ወይም ስብከቱን ባዘጋጀነው ቅደም ተከተል መሠረት÷ አጽንዖት የምንሰጠውን እየሰጠን መቀጠል ነው::

ልክ በስብከታችን አቀራረብ ስልትና ዘዴ እንደመለያየታችን መጠን በዚያው ስልትና ዘዴ ልንሠራበት እንችላለን:: የዚህ የልምምድ ማብራሪያ ዋና ዓላማ በአንድ ዐይነት ስልት እንድንገደብ ሳይሆን እያንዳንዱን ጥቅስ ለማብራራት ሳንቸገር እንዴት አድርገን በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልና ዐውደ ሐሳብ ልንሠራ እንደምንችል ለማሳየት ነው::

፱

## ብሉይ ኪዳንን ማብራራት (2)

### የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ሰባኪዎች

የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍተ ነቢያት በምናብራራበት ጊዜ በሰፊው የምንሠራበት፥ እነዚያ ጥንታውያን ሰባኪዎች የሰበኩትን ወይንም የጻፉትን መልእክት ነው። የአንድ ነቢይ መጽሐፍ ብዙ ጊዜ ተራኪ መጽሐፍ ባለመሆኑ ሥራው የታሪክ መጽሐፍን ከማብራራት የበለጠ ከባድ ነው። ምክንያቱም በእያንዳንዱ ጥቅስ በተናጠል ማብራሪያ በመስጠትና በየመሐሉ ላሉት ሁኔታዎች የራሳችንን ማጠቃለያ በመስጠት ማቅረብ ስለማንችል ነው። ስለዚህ የአንድን ነቢይ ስብከቶች አብራርቶና ተርጉሞ ለማቅረብ አብዛኛውን የመጽሐፉን ክፍል ተንትኖ ማብራራትን ያሻል። ባጠቃላይ አድማጮቻችን ከነቢያት መጻሕፍት ጋር ያልተዋወቁ ናቸው፤ እናም ሳንነጋገርባቸው የምናልፋቸውን ክፍሎች ሊያውቋቸው ይችላሉ ብለን መገመት የለብንም። አብዛኞቹን ጥቅሶች ማብራራት ይገባናል።

ደቂቅ ነቢያትን በተመለከተ (ወይም መለስተኛ መጠን ላላቸው እንደ መጽሐፈ መክብብና ማሕልየ መሓልይ ያሉትን)፥ መጽሐፉን በሙሉ ማዳረስ እንችላለን። እነዚህ መጻሕፍት በመካከለኛ ግምት ወደ ስድስት ምዕራፎች ገደማ ቢሆኑ ነው፤ እናም ልክ የአዲስ ኪዳንን መልእክቶች ባብራራንበት ሁኔታ በዝርዝር ባይሆንም በአብዛኛዎቹ ጥቅሶች ላይ ማብራሪያ መስጠት እንችላለን። እንደ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስና ሕዝቅኤል ረዘም ያሉትን መጻሕፍት ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰፊው እያብራሩ ማቅረብ ያስቸግራል። እዚህ ላይ እንደ አሠራራችን ትንቢተ ኢሳይያስን ሞዴል አድርገን የምንጠቀምበት ቢሆን ስለትናንሾቹ ደግሞ ደቂቅ ነቢያትን ምሳሌ ማድረግ እንችላለን። ረዘም ያለ መጽሐፍ እንዴት እንደሚብራራ ካወቅን አጭሩን መጽሐፍ ማብራራቱ አያዳግተንም።

### የራሳችን ግንዛቤ

አንድን መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለትምህርት ከማቅረባችን በፊት አስቀድመን በሚገባ ማጥናት እንዳለብን እናውቃለን። ትንቢተ ኢሳይያስን በተመለከተ ለማስተማር ከማቀዳችን በፊት እንኳ መጽሐፉን አስቀድመን ለብዙ ወራት ማጥናት ሊኖርብን ይችላል። ነገር ግን እንደ ትንቢተ ሶፎንያስ ባለው ትንሽ መጽሐፍ ላይ ሁለት ወይም ሦስት ስብከቶችን ለማዘጋጀት ችግር አይኖርብንም። ከመጽሐፉ ጋር አስቀድመን ብንተዋወቅም ባንተዋወቅም ቀደም ብለን ለበርካታ ሳምንታት ዝግጅት ብናደርግ ይህን መጽሐፍ ያለ አንዳች ሥጋት ማስተማር እንችላለን። ትንቢተ ኢሳይያስን በተመለከተ ግን መጽሐፉን በሙሉ በሚገባ አጥንተን ካልጨረስን በስተቀር አውቀነዋል ብለን በድፍረት በመነሣት ብቻ መስበክ የማይታሰብ ነው። ይህን መጽሐፍ ለማስተማር ከማቀዳችንና ሥራ

ከመጀመራችን በፊት ይዘቱንና ሥርዓተ ክፍፍሉን ደኅና አድርገን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ይህን በምናደርግበት ጊዜ የመጽሐፉን መልእክት ግልጽ አድርገን ተቀባይነት ባለው መንገድ ለምእመኑ ማስተማር እንችላለን፡፡

ለአሁኑ መለማመጃ መጽሐፉን የማጥናት ከባድ ሥራ እንደሠራን እንገምት፡፡ ይህን ካደረግን ከመጽሐፉ ይዘት ጋር ተዋውቀናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ዕቅዳችንን አውጥተን ማስተማራችንን መጀመር አለብን፡፡

እዚህ ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ የማስተማር ፕሮግራም ምን ያህል ብዛት ያለው ስብከት ሊሰጠን እንደሚገባ ወሳኙ እርሱ ነው፡፡ መጽሐፉን ለስድስት ወራት በየእሑዱ የምንሰብክ ከሆንን ዝርዝር ሐሳቡን አዘጋጅተን በማብራራት ልንሰብክ እንችላለን፤ ጉባኤው ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ ለመከታተል ይቸገር ይሆናል፡፡ በመጽሐፉ ላይ ለሦስት ወራት ተከታታይ ስብከት በማድረግም እንኳ የምእመኑ የማድመጥ ትእግሥት ምን ያህል እንደ ሆነ መገመት እንችላለን፡፡ እንግዲህ ለዚህ ልምምድ ሌላው ዘዴ የመጽሐፉን የሐሳብ ፍሰት ጠብቀን ሁለት ላይ መክፈል፥ ለእያንዳንዱ ክፍል ዕቅድና ዝግጅት የተወሰኑ ወራትን መውሰድ፥ ከዚያም ክፍሎቹን ለያይቶ ለሚዎቹን በሚስብ ዘዴ ማዘጋጀትና ማቅረብ ነው፡፡

በሚቀጥለው የምሳሌ አሠራር ላይ መጽሐፉን በዐሥራ ሁለት ስብከቶች ከፋፍለን እንደምናዘጋጅ አድርገን እንገምት፡፡ እነዚህ ሰባቱ ከምዕራፍ 1-39 ያሉትን፥ አምስቱ ደግሞ ከምዕራፍ 40-66 ያሉትን ክፍሎች እንዲሸፍኑ እናደርጋለን፡፡ እንደገናም ስብከቱ በሠላሳ ደቂቃ ውስጥ እንዲተመን እናቅዳለን፡፡

## የመጽሐፉ ዝግጅት ምን መሆን እንዳለበት

ምን ጊዜም ቢሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መካከል አንዱን ማጥናት ስንሻ ትኩረታችን የጸሐፊውን ዓላማ በመረዳትና ይህንንም ዓላማውን በመሐፉ ውስጥ እንዴት እንዳሳደገው መመልከት ይሆናል፡፡ መጽሐፉን ለማብራራት በምንፈልግበት ጊዜ፥ በተቻለ መጠን፥ ጸሐፊው ለመጽሐፉ የሰጠውን ቅርጽ ተከትለን መሥራት የግድ ይለናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ከምናገለግልባት ቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብር ውስንነት የተነሣ፥ የመጽሐፉን ፍሬ ነገሮች ከስብከታችን ጋር በሚስማማ ሁኔታ አቀናጅተን መጠቀም ይኖርብናል፡፡

እንዲህ ማለትም፥ ኢሳይያስን በተመለከተ፥ ከጽሑፎቹ ውስጥ ጥቂቱን ክፍል መርጠን እንጠቀማለን ማለት ነው፤ ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ የጸሐፊውን ዓላማና የጽሑፉን ትርጉም የማናፋልስ ታማኞች ሆነን መገኘት የግድ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ አንደኛው መንገድ በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጹትን የድርጊት ወይም የክሥተት ዘመናት ቅደም ተከተል በመጠበቅ ስብከቶቻችንን ማቀድና ማዘጋጀት ነው፡፡ ምክንያቱም የትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፎች የታሪኩን

ዘመናት ቅደም ተከተል ጠብቀው የተጻፉ አይደሉም። ሰዎች መጽሐፉን ሲያነቡት ይከብዳቸዋል። ነገር ግን በሁኔታዎች ወይም ክስተቶች ቅደም ተከተል መሠረት ብናጠናው፥ ሰዎች መጽሐፉን እንዲገነዘቡት ልናግዛቸው እንችላለን። ምዕራፎቹን በመከፋፈል ስናደራጅ፥ ሐሳባቸውን አጉል እንዲቋረጥ ሳናደርግ አንድነታቸውን በመጠበቅ መከፋፈል ይኖርብናል። የሚከተለው የአዘገጃጀት መርሐ ግብር በዐሥራ ሁለት ስብከቶች ውስጥ የሚጠቃለሉትን ምዕራፎች ያመለክታል።

## በኢሳይያስ 1-39 ላይ የሚዘጋጁ ሰባት ስብከቶች

አብዛኛውን ጊዜ፥ የመጽሐፉን የታሪክ መነሻ በመግለጽ እንጀምራለን። አድማጮቻችንን በኢሳይያስና በመጽሐፈ ነገሥት መካከል ያለውን ተያያዥነት ወደሚያመለክቷቸው ምርጥ ጥቅሶች መምራት አለብን። በመጽሐፉ ዙሪያ ያሉትን ሁኔታዎች አድማጮቻችንን እንዲገነዘቧቸው ካደረግን በኋላ ምዕራፍ አንድን ማብራራት እንጀምራለን። ምናልባት በኢሳይያስ መጽሐፍ ላይ አንድ ልዩነት ማድረግ እንችል ይሆናል። ይህም መጽሐፉን ለማብራራት በምንመርጠው ዘዴ ላይ የተደገፈ ነው። ኢሳይያስ በዘመኑ የነበሩትን ነገሥታት የሚገልጽ ቢሆንም እኛ ደግሞ የተጠቀሱትን ነገሥታት ሁኔታዎች በአንድ ጊዜ በሰፊው ማብራራት ብንሞክር አድማጩን ግራ እናጋባለን። መጽሐፉን እያብራራን ስንቀጥል፥ ዝርዝር ሐሳቦችን በየደረጃው እንደርስባቸዋለን። ለእያንዳንዱ ክፍል ግን መነሻ መሠረት (መግቢያ) መስጠት እንችላለን።

በምዕራፉ መክፈቻ ላይ ስማቸው ተጠቅሶ የነበሩት ነገሥታት፥ ያዝያንና ኢዮአታም እንደገና የሚጠቀሱት አልፎ አልፎ ነው። ምንም እንኳን ኢሳይያስ ከምዕራፍ 1-6 ድረስ በንግሥናቸው ዘመን የይሁዳን ሁኔታ ቢገልጥም፥ በተቀረው የንግሥና ዘመናቸው ስለሆኑት ድርጊቶች ግን ዘርዝሮ ለማቅረብ አልተጨነቀም። እነዚህ ስድስት ምዕራፎች የመጽሐፉን ገጽታ ይጠቁሙናል፤ የመጀመሪያውን ስብከታችንን ይዘትም ያቀርቡልናል።

ኢሳይያስ በዋናነት ያቀረባቸው ሁለቱ ነገሥታት፥ አካዝና ሕዝቅያስ ናቸው። ከምዕራፍ 7-12 ያለው ክፍል የሚናገረው በተለይም ስለ ንጉሥ አካዝ ንግሥና ነው፤ ታሪኩ በጥንቃቄ ተብራርቶ ሊቀርብ ይገባዋል። ዝርዝር ሐሳቦች የሚገኙት ከምዕራፎቹና ከነገሥታቱ ነው። እኛም ከእነዚህ ምዕራፎች ሁለት ስብከቶችን ማውጣት እንችላለን።

የኢሳይያስ ምዕራፍ 28-39 ዋናው ዓላማ የሕዝቅያስ ንግሥና ነው፤ በእነዚህ ክፍሎች ላይ ያተኮሩ ሁለት ተጨማሪ ስብከቶችን ማዘጋጀት እንችላለን። (በዚሁ ክፍል ውስጥ ስለ ድነትና ስለ ፍርድ የሚናገሩ ሁለት ምዕራፎች አሉ፤ ነገር ግን በጊዜ እጥረት የተነሣ ስብከት ልናዘጋጅባቸው አንችልም)። በእነዚህ

ምዕራፎች ውስጥ ያሉ ሐሳቦች በመጻሕፍተ ነገሥት ውስጥም ይገኛሉ፤ በምዕራፎቹ በራሳቸው ውስጥ እንደሚገኙ ሁሉ በታሪካዊ ማውጫም ይገኛሉ።

አሁን ከ13-27 ያሉ ምዕራፎች ይቀራሉ። በመጨረሻ ላይ ያሉት አራት ምዕራፎች፥ ይህ ክፍል ለተለያዩ ሕዝቦች የመልእክቶች ስብስብ ነው። (በመጨረሻው ላይ ያሉት አራት ምእራፎች እንደ ገና ስለ ፍርድና ድነት ሰፋ ያሉ ሐሳቦችን ይዘዋል፤ ሆኖም ጊዜ ስለማይፈቅድ ልንነጋገርባቸው አንችልም)። በዚህ ክፍል ላይ ሁለት መልእክቶችን ብቻ ማዘጋጀት እንችላለን። ለአድማጮቻችን ነገሮችን ለማቃለል በምዕራፎች ቅደም ተከተል ላይ በማተኮር ፈንታ በታሪክ አቀማመጣቸው ተራ ልንመድባቸው እንችላለን። በመጀመሪያ በአካዝ፥ ከዚያም በሕዝቅያስ ዘመን ስለ ነበሩት ሕዝቦችና በመጨረሻም ስለ ባቢሎናውያን ዘመን መናገር ይቻላል። ይህ የመጨረሻው ቡድን ከምዕራፍ 1-39 ያሉትን ሐሳቦች ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያደርሳቸውና ከምዕራፍ 40-66 ላሉት ሐሳቦች መንገዱን ያዘጋጃል።

## በኢሳይያስ ምዕራፍ 40-66 ላይ የተመሠረቱ አምስት ስብከቶች

ከምዕራፍ 39-40 መካከል የ150 ዓመታት ክፍተት አለ። ትዕይንቱ በኢሳይያስ ጊዜ ከነበረችው ኢየሩሳሌም በባቢሎን ወደ ነበረው የይሁዳ ምርኮ ይለወጣል። እግዚአብሔር የባቢሎንን ውድቀት እያዘጋጀ፥ ከዚያም የአይሁድን ሕዝብ ከምርኮ ነጻ የመውጣትንና የኢየሩሳሌምን ዳግም ግንባታ ጊዜ እያመቻቸ ነው። ከምዕራፍ 40-48 ያለው ስለ እነዚህ ጉዳዮች በተለያዩ መንገዶች ይናገራል በእነዚህ አምስት ቡድኖች ውስጥ ለመጀመሪያው ስብከት ነጥቦችን ያበረክታል።

በዚህ በመክፈቻ ክፍል ውስጥ ስለ እግዚአብሔር አገልጋይ ከአራቱ መዝሙራት የመጀመሪያውን እናገኛለን ሆኖም ስለ አገልጋዩ በስፋት ለመነጋገር በቂ ጊዜ የለንም። ያም ሆነ ይህ ከምዕራፍ 49-55 ባለው አዲስ ክፍል ላይ በምንነጋገርበት ጊዜ በዚህ መዝሙር ላይ አስተያየት መሰንዘር እንችላለን። ይህ ክፍል የሌሎች ሦስት አገልጋዮችን መዝሙራትም ይጨምራል፤ ይህ በሁለት ስብከቶች ውስጥ ሊወሳ ይችላል። ከቀሩት ሁለት መዝሙራት መካከል አንደኛው የተቋቋመውን ሕዝብ ሕይወት (ምዕራፍ 56-60)፥ ሌላው ደግሞ እግዚአብሔር በእውነት የእርሱ ለሆኑት ያዘጋጀውን የከበረ ተስፋ (ምዕራፍ 61-66) ያሳያል።

## የመክፈቻውን ስብከት ስለ ማቀድ

የምሳሌ አጠቃቀማችን በመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሁለት ስብከቶች ላይ ራሱን ይወስናል። በኢሳይያስ ምዕራፍ 1-6 ያለውን በምንመለከትበት ጊዜ ስድስት ምዕራፎችን (128 ጥቅሶችን) እንዴት በሠላሳ ደቂቃ ውስጥ እንደምንሸፍን ሊገርመን ይችል ይሆናል። እዚህ ላይ እያንዳንዱን ጥቅስ አንብበን ማብራራት እንደማንችል ግልጽ ነው፤ ደግሞም በምዕራፎቹ ላይ ቅኝት በማድረግና ጥቅሶቹን

በተናጠል በማንበብ እንዲሁም በመሀከል ያለውን ስፍራ በራሳችን ማጠቃለያ ሐሳብ መሙላት አንችልም። እየሠራን ያለነው በትንቢት መጽሐፍ ላይ የሚዘጋጅ ስብከት እንጂ ተራኪ አይደለም። ጽሑፉ የተዘጋጀውም በሥነ ግጥም እንጂ በስድ ንባብ አይደለም። የስብከቱ መልእክት ለአድማጮች እንዲናገር ከፈለግን መገለጽ አለበት። ያሉትን የመልእክት ክፍሎች በስብከታችን ውስጥ ማካተት ስለማንችል ሁሉንም ባይሆን የነቢዩን መልእክት የሚወክለውን ክፍል መውሰድ አለብን።

ኢሳይያስ ምዕራፍ 1-6 ያለውን በተመለከተ በይሁዳ የነበረውን ሁኔታና እግዚአብሔር ኢሳይያስን ለመልእክተኛነት የጠራበትን ምክንያት በሚገልጹት ክፍሎች ላይ ማተኰር አለብን። ይህ የመጽሐፉ አካሄድ እንዴት እንደ ሆነ የሚያሳየን ከመሆኑም በላይ በዚህ ጊዜ ለዛሬ የመመሪያ ትምህርት ይሰጠናል።

የእነዚህን ምዕራፎች ከፊሉን ሙሉ በሙሉ ስለምናስቀር፥ በተለይም ስለ ኢየሩሳሌምን ክብር የሚናገረውን ለማስቀረት መወሰን አለብን። ይህ ርእስ ወደ ኋላ ላይ በሚመጡት ምዕራፎች ውስጥ የታወቀ ስፍራ እንዳለው እናውቃለን፤ ስለዚህ ወደነዚያ ምዕራፎች ስንደርስ እንነጋገርበታለን። በዚህ ሁኔታ ተጠንቅቀን በምንመርጠው ርእስ አማካይነት በእያንዳንዱ ስብከት ላይ የተለያየ ትኵረት እንዲኖረን ያደርገናል፤ ያም ሆኖ መላውን መጽሐፍ ማዳረስ እንችላለን። ምንም እንኳን ሰዎች እያንዳንዱን ስብከት ለመስማት ባይችሉም የሚሰሟቸውን ስብከቶች ግን እያንዳንዳቸውን መገንዘብ አለባቸው። ይህን ለማስቻልም እያንዳንዱ ስብከት በየራሱ እንዲገባ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። ተከታታዩን ስብከት የመስማት ዕድል ካላቸው መላውን መጽሐፍ የማወቅ አጋጣሚ ይኖራቸዋል።

ከመክፈቻዎቹ ስድስት ምእራፎች መካከል የምንነጋገርባቸውን አራቱን ክፍሎች እንመርጣለን፤ እያንዳንዱን ክፍል ስንመለከትም ጉባኤው ከእኛ ጋር እንዲያነብ እንጠይቃለን። የተለየ አቀራረብ ሊኖረን ስለሚገባ አራቱንም ክፍሎች በአንድ ዓይነት መንገድ መተግበር የለብንም። ብዙ ሰዎች በማብራሪያዊ የአሰባበክ ዘዴ ላይ የተዛባ አስተያየት አላቸው። ይህ አስተሳሰብ የሚከሰትባቸው በተለይ ሰባኪው ብዙ ተከታታይ ስብከቶችን ወይም ትልቅ መጽሐፍን በተመለከተ የሚሰብክ ከሆነ ነው። በመጀመሪያው ስብከታችን አድማጮቻችንን እንዳናሰለች መጠንቀቅ ያሻናል። ስድስቱን ምዕራፎች ለመሸፈን ይህ ተጨማሪ ምክንያት ነው። ሰባኪው በመግቢያው ላይ ረጂም ጊዜ ቢያሳልፍ ወይም በመግቢያ ጥቅሶች ላይ ብዙ ቢናገር አድማጮች ይሰለቻሉ። አድማጮቻችንን ቶሎ ወደ መጽሐፉ እንዲገቡ ብንረዳቸው ትምህርቱን ይገነዘባሉ፤ የበለጠ ለመስማትም ይነሣሣሉ።

## ተግሣፀ እግዚአብሔር

ነቢያት ከተለያየ የሕይወት፥ የኑሮና የሙያ አካባቢዎች የመጡ ነበሩ። አንዳንዶቹ ከባላገር፥ ሌሎች ከከተማ የመጡ፥ አንዳንዶች ገበሬዎች፥ የተቀሩት

የነገሥታት ባለሟሎች ነበሩ:: ኢሳይያስ የታወቀ መሪ፥ የበርካታ የይሁዳ ነገሥታት አማካሪና የኢየሩሳሌም ከተማ ነዋሪ ነበር:: በምዕራፉ መክፈቻ ላይ በስማቸው የተጠሩትን ነገሥታት ለአድማጮቻችን ልናመለክታቸው እንችላለን፤ ነገር ግን ስለ እነርሱ ተናግረን ማቆም የለብንም:: ስለ አካዝ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ፥ ከዚያም ስለ ሕዝቅያስ እንደምንናገር መግለጽ ይጠበቅብናል:: ከዚሁ ጋር በማያያዝ የእስራኤል ሕዝብ ሁለት መንግሥታትን በመመሥረት እንደተከፈለ፥ በዚህ ምክንያት ሰሜኑ ክፍል የእስራኤል መንግሥት ሲባል የደቡቡ ደግሞ የይሁዳ መንግሥት መባሉን ማሳወቅ ያሻል፤ ይህም በሚቀጥለው ስብከት ወቅት በበለጠ ይብራራል:: ለአሁኑ የምናስታውሰው ኢሳይያስ ትኩረት ሰጥቶ የሚናገረው፥ በተለይ ስለ ይሁዳ ዋና ከተማ፥ ስለ ኢየሩሳሌም መሆኑን ነው::

አድማጮቻችን ከዚህ በፊት ስለ ኢሳይያስ የሚያውቁት ነገር ይኖራል፤ ቢያንስ የመጀመሪያውን የመክፈቻ ምዕራፍ አንብበው ይሆናል:: ለአንዳንዶቹ ነገሩ አዲስ ቢሆንም ለአብዛኛዎቹ ግን የምዕራፉ የመጀመሪያ ክፍል በእጅጉ የታወቀ ሊሆን ይችላል:: ይህ ከሆነ ጥቂት ማብራሪያ ብቻ ያስፈልጋል፤ ስለዚህ የመጀመሪያዎቹን ሃያ ጥቅሶች መርጠን የብሉይ ኪዳኑ ነቢይ ትንቢቱን በተናገረበት ሁኔታ በማንበብ የመጽሐፉን መንፈስ ለአድማጮቻችን ማስተዋወቅ እንችላለን:: ቀደም አድርገን የተወሰኑ ጥቅሶችን እንመርጥና ከዚያ በኋላ ከአስተያየት ጋር እናስተዋውቃለን፤ ቀጥለን በጋለ ስሜት በንባብ እናሰማለን::

የመክፈቻው ገጽታ፥ የፍርድ ድባብ ያለበት ነው፤ ይሁዳ በእግዚአብሔር ላይ ከማመፁና ምስጋና ቢስ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ይከሰዋል:: የይሁዳ ሕዝብ ለእግዚአብሔር ካለው ስሜት ይልቅ እንስሳት የጌቶቻቸውን ወሮታ ያውቃሉ ይላል፤ (ኢሳ. 1፥2-3):: ኀጢአተኞች ስለ ሆኑ እርሱን ናቁት፤ (ቁ. 4):: እግዚአብሔር እስኪቄስሉ ድረስ ቀጣቸው፤ እነርሱም አልገባቸውም፤ (ቁ. 5-6):: አገራቸውን የሚያጠፋ ጠላት ላከባቸው፤ ግን አልተለወጡም፤ (ቁ. 7)::

ሌሎችን የእግዚአብሔርን ክሶች ለመመልከት እንድንችል ጥቂት ጥቅሶችን እናልፋለን:: ሕዝቡ በሚያቀርቡት መሥዋዕትና የሃይማኖት በዓላት እግዚአብሔር የሚደሰት ይመስላቸው ነበር፤ ሆኖም መላው ሕይወታቸው በኀጢአት የረከሰ ስለ ነበር እግዚአብሔርን ያስደስተዋል ብለው የሚፈጽሙት ተግባር ሁሉ በእርሱ ፊት የተጠላ ነበር፤ (ቁ. 10-15 ይመ.):: እግዚአብሔር ከእነርሱ ይፈልገው የነበረው የባሕርይ ለውጥ እንጂ ተጨማሪ ሃይማኖታዊ ድርጊቶችን አልበረም:: ስለዚህ፥ ከኀጢአት መመለስ፥ ርኅራኄ ማድረግ፥ በዕለታዊ ኑሮቸው ፍትሕን መለማመድ አለባቸው፤ (ቁ. 16-17):: ምሕረትን ለማግኘት ጊዜው ያለፈ አይደለም ከኀጢአታቸውና ከዐመፃቸው ለመመለስ ፈቃደኞች ከሆኑ እግዚአብሔር ይቅር ሊላቸው ፈቃዱ ነበር፤ (ቁ 18):: አማራጩን መንገድም ነግሯቸዋል፤ (ቁ. 19-20)::

ይህ አጭር ክፍል ከአምስት ደቂቃ በላይ መነበብ የለበትም። ክፍሉን በአጽንዖት ስናነበው አድማጮቻችን እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የተናገረውን እንዲገነዘቡ ከመርዳታችንም በላይ፣ ለእኛም የሚናገረውን ልብ እንላለን። ገና ወደሚቀጥለው ተጨማሪ ምንባቦች ስለምንገዝ በዚህ ላይ ሰፋ ያለ ጊዜ ማሳለፍ አይኖርብንም። የእግዚአብሔር ቃል ራሱ እንዲሠራ ልንተወው እንችላለን።

## ኀጢአት ወዴት ያመራል?

ኢሳይያስ በምዕራፍ 3 ላይ ስለ ኢየሩሳሌም ውድቀት ያለውን መልእክት በሥዕላዊ መንገድ ባወጀበት ጊዜ ኢየሩሳሌም አልጠፋችም ነበር፣ ሆኖም አንድ ማኅበረሰብ ራሱን ወዳድ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ ኅብረተሰብ መጨረሻ ምን እንደሚሆን ለይሁዳ ሰዎች፥ (ለእኛም) ለማስገንዘብ ፈለገ።

ልክ በምዕራፍ 1 ላይ ያደረግነውን ተግባር በዚህ ክፍል ላይም መፈጸም እንችላለን፣ ይሁን እንጂ ረጃጅም የሆኑትንና ለማብራራትም ጊዜ የሚጠይቁትን ጥቅሶች መዝለል ይኖርብናል። ይህ ምዕራፍ እንዳለፈው ምዕራፍ በተለይም ለመንፈሳዊ ጉዳዮች ትኩረት ሰጥተው የሚናገሩ ጥቂት ነጥቦችን ይዟል። ምንም እንኳን ምዕራፉን እያነበብን ወደ ፊት በምንቀጥልበት ጊዜ አንዳንድ ልብ ልንላቸው የሚገቡ የማኅበራዊ ኑሮ ክፋቶች ቢተኮሩበትም፥ በተግባር ላይ ሊውል የሚችለው ሐሳብ የሚገኘው ከአጠቃላይ የምዕራፉ መልእክት ላይ ነው። ይህን ምዕራፍ በምናጠናበት ጊዜ አጻጻፉና ሐሳቡ በጣም ገላጭ የሆነና የሚስብ ነው፣ ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ በጽሑፉ አማካይነት ምን ሊያወሳን እንደ ፈለገ መገመት አያስቸግረንም። ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረውን ሐሳብ አጥንተን፥ መልእክቱ ከዛሬው ሁኔታ ጋር ያለውን ግንኙነት ብናብራራላቸው፥ አድማጮቻችን ከሕይወታቸው ጋር በማዛመድ ሊቀበሉትና ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ማሰብ ይኖርብናል።

በኢሳይያስ ሥዕላዊ አጻጻፍ መሠረት መንግሥቱ ሲወድቅ እንደ ምግብና ውሃ ያሉ መሠረታውያን ነገሮች እጥረት እንደሚኖር ይናገራል፤ (ቊ 1 ይመ.)። ክፉ ወይንም መልካም ሆኖ አገሪቱን ሊመራ የሚችል መሪ አይገኝም፣ (ቊ 2-3)። ሕገ ወጥነት ይበዛል፤ ሥልጣንም ባልበሰሉ ወጣቶች እጅ ይወድቃል፤ (ቊ 4-5)። ከቊጥር 6-7 ባለው ክፍል፥ ሕገ ወጥነትና ድብልቅነት በነገሠባት ከተማ ሕግና ሥርዓትን የሚያስጠብቅ ሰው ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ ከንቱ እንደ ሆነ እንመለከታለን፤ እነዚህን ጥቅሶች አብራርቶ ለማስተማር ጊዜ ያጥረናል።

ከተማይቱ የፈረሰችበት ምክንያት፥ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ችላ ብሎ ስለ ዘነጋው መሆኑን አድማጮቻችን እንዲያስተውሉ ትኩረት ሰጥተን ልናሳስባቸው ይገባል፤ (ቊ. 8 ይመ.)። በቊ. 9 መጀመሪያ ላይ ስለ ሞራል ብቃታቸውና ኑራ ስለ መንዛታቸው ስለ ብልሹ ጠባያቸው መታበያቸውን ለአድማጮች ማሳወቅ አለብን። እነዚህ የተነገሩ ትምህርቶችና ማስጠንቀቂያዎች ከዛሬው ኅብረተ ሰብ

ሕይወት ጋር በምን ሁኔታ እንደሚያያዝ በጥቅሶቹ ላይ የእኛን ማብራሪያ በጥቂቱ በመጨመር መግለጽ አድማጩን ይረዳል።

ነዋሪዎቹ ለሕዝቡ ውድቀት ምክንያት መሆናቸውን እግዚአብሔር ወቀሳ ባቀረበበት በቍጥር 12 ሁለተኛ ክፍል ላይ የሚገኘው ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ከበድ ያለ ግምት የሚሰጠው ነው። መሪነት ሥልጣንና ማዕረግ እንደማምጣቱ መጠን ኀላፊነትንና ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል ለአድማጮቻችን ማስገንዘብ አለብን። ይህም በፖለቲካው ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያንም ይታያል በቍ 12 ላይ የተገለጸው ማሳሰቢያ በአመራር ደረጃ ላይ ያለነውን ሁሉ ይመለከተናል።

እግዚአብሔር ጠበቃ የሌላቸውን ዜጎች የሚያጠቁትንና ራሳቸውን ለማበልጸግ በሥልጣናቸው የሚጠቀሙትን አጥብቆ ይገሥጻቸዋል። ነቢዩ በግልጽ የሚናገረው ስለ ብሔራዊ ፖለቲካ መሪዎች ነው፤ (ከቍጥር 14-15 ይመ.)። አያይዞም ውድ የሆነ ልብስ በመልበስ ከልክ በላይ ስለሚያጌጡና ከዚህ የተነሣም ስለሚታበዩ፥ የኋላ ኋላም ውድቀታቸው ስለሚከተላቸው፥ ስለሚስቶቻቸው ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤ (ቍ. 16-17 ይመ.)። ቍ. 18-25 ስለ ሀብት ከንቱነት፥ ይህ ሀብት ጠፍቶ በድኽነትና በውርደት እንደሚተካ ያስጠነቅቃል።

ስለ ምዕራፍ 3 ስንነጋገር በገለጻችን ላይ ብሩህና ሕይወት ሰጪ የሆነ ትምህርት ልናክልበት እንችላለን። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳደረገው ሁሉ የእኛም ዐላማ ራሱን በሚወድና ፍትሕን በማይሻ ኅብረተሰብ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚወርድ ማስገንዘብ ነው። ትምህርታችን ከዘመናችን ሁኔታ ጋር ያለውን ትሥስርም ማስገንዘብ ይገባናል፤ (ቍ. 8፥9፥12 እና 15 ይመ.)።

### የተወሰኑ ኀጢአቶች

ነቢዩ ኢሳይያስ ከምዕራፍ 1-3 ድረስ ያቀረበውን፥ ግልጽና ሥዕላዊ ባሕርይ ያለውን ጽሑፍ ለማብራራት ከዐሥራ አምስት ደቂቃ በላይ የረዘመ ጊዜ አልወሰደብንም ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ አድማጮቻችን በመጽሐፉ አቀራረብ ሳይማረኩና በመልእክቱም ልባቸው ሳይነካ አልቀረም። አሁን ደግሞ ለኢየሩሳሌም ርኩሰትና ውድቀት፥ ለፍርድ መምጣት ምክንያት ስለ ሆኑት አምስት ኀጢአቶች ወደ ተጻፉበት ወደ ምዕራፍ 5 እናልፋለን።

በኋላ ላይ ከእነዚህ ኀጢአቶች መካከል ጥቂቶቹን እናነሣለን፤ በወደፊቶቹ ስብከቶቻችን ውስጥ ግን እንነጋገርባቸውም። ይህም ተግባር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማመሳከሪያዎችን እንዴት እንደምንመርጥና እንደምንጠቀምባቸው ያሳያል። ይህን ስናደርግ ለስብከት በሚስማማ ዘዴ እንጠቀምበታለን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የጸሐፊውን መልእክት በማስተላለፍ ደረጃ ታማኞች መሆን ይኖርብናል። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በኋላ ላይ ለምናዘጋጀው ስብከት ርእስ ጕዳይ እንዲሆነን

ሰለምንፈልግ ባሁኑ ስብከታችን ስለ እስራኤል ክብር የሚናገረውን እናልፈዋለን:: በተመሳሳይም በሚቀጥለው ስብከታችን ስለ ማኅበራዊ ክፋቶች የተጠቀሱትን ሐሳቦች እንዘላቸዋለን፤ ምክንያቱም ያሁኑ ስብከታችን ርእሰ ጉዳዮች ስለሆኑ ነው::

ቀደም ሲል ጥቅሶቹን አንብበን አስተያየት ሰጥተናል:: በዚህ ምዕራፍም ጥቅሶቹ ተነበው አስተያየት እንሰጠባቸዋለን:: ስለ አምስቱ ኀጢአቶች የሚናገሩት ጥቅሶች፥ ሁሉም «ወዮላችሁ...» ወይም «ጠፍታችኋል!» በማለት ያስጠነቅቃሉ::

ስለ መጀመሪያው ኀጢአት እንድናስተውል ቊ 8-9 እናነባለን:: ባለጠጎች ለደኻው ኅብረተ ሰብ አራጣ ያበድራሉ፤ ድኾቹ ዕዳቸውን መክፈል በሚያቅታቸው ጊዜ መሬታቸውን ይወስዱባቸዋል:: እግዚአብሔር ጨካኞች በሀቅ ያላገኙትን ሀብታቸውን ያሳጣቸዋል:: የጥቅሶቹን መልእክቶች ከጊዜያችን ጋር እናዛምዳለን::

ነቢዩ ራሳቸውን ለማስደሰት ስለሚኖሩት ሰዎች የተናገረባቸውን ጥቅሶች፥ ቊ. 11-12ን ልናልፋቸው እንችላለን:: ስለ እነዚህ ሰዎች ክፉ ጠባይ የሚናገረው ብዙ ገንዘብ ስለሚያባክኑ ብቻ ሳይሆን፥ ይህ ከንቱ ጠባያቸው እግዚአብሔርን ወደ አለማወቅ ስለሚያደርሳቸው ነው:: ይህ ድርጊት ከዛሬው ሁኔታ ጋር ሊመሳሰል እንደሚችል አሁንም ግልጽ ነው::

ቊ. 18-19ን ስንመለከት ነቢዩ «ኀጢአትን በማታለል ገመድ ለሚስቡ፥ በደልንም በሠረገላ ማሠሪያ ለሚጎትቱ» ይላል፤ እነዚያ ሰዎች በሚሠሩት ኀጢአት ይመኩ፥ እግዚአብሔር ኀጢአት እንዳይሠሩ እንዲያደርጋቸው ይፈታተኑት ነበር::

አራተኛው ምሳሌያችን ትንሽ ማብራሪያ ብቻ ከሚያስፈልገው፥ ከቊጥር 20-21 ላይ ይገኛል:: ሰዎች የእግዚአብሔርን ዕውቀት ይቃወማሉ፤ ሁሉን እንደሚያውቁና እግዚአብሔር እንደማያስፈልጋቸው ይገምታሉ::

ይህን ክፍል ለማጠቃለል ከቊ. 22-23 ያለውን እናነባለን:: ነቢዩ ስለ ሀብታሞችና ኀያላን ማኅበራዊ ሕይወት በአስገራሚ መንገድ ያስረዳል:: «የወይን ጠጅ ለመጠጣት ጀግኖች» ፥ «የሚያሰክር መጠጥ ለመደባለቅ ብርቱዎች»፥ ፍትሕን ለማድረግ ግን ደካሞችና ፈሪዎች» ናቸው ይላል::

## ቀዳሚው ሥራ

በትንቢተ ኤርምያስና ሕዝቅኤል ላይ የእግዚአብሔር አጠራር ከምዕራፍ 1 ይጀምራል:: የኢሳይያስን አጠራር ግን ከምእራፍ 6 በፊት አናገኝም:: ምናልባት ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት በመጀመሪያዎቹ 5 ምዕራፎች ላይ እንደምናነበው የይሁዳ ሁኔታ እጅግ የከፋ፥ የወደፊቱ የኢሳይያስ ተግባር ደግሞ እጅግ ከባድ ስለሚሆን ሳይሆን አይቀርም::

ምዕራፍ 6 በአድማጮቻችን ዘንድ የታወቀ ቢሆንም ባይሆንም፥ እያንዳንዱን ቃል ማንበብ አንችልም:: ይህን ክፍል ለማብራራት ምናልባት አጽንዖት ልንሰጣቸው የምንፈልጋቸውን ጥቅሶች ማንበብና በየመካከሉ የራሳችንን ማጠቃለያ እየሰጠን ማለፍ እንችላለን:: ስለ ቅዱስ እግዚአብሔር ከፍ ብሎ በክብር መታየት የሚገልጸውን ክፍል ጠቅለል አድርገን በራሳችን አባባል እናቀርበዋለን፤ (ቊ. 1-4)፥ ቊ. 5ን እንድናነብ ይመራናል:: ኢሳይያስ የረከሰ ሰው መሆኑን ይገልጻል፤ ይህን ያለበት ምክንያትም ከረከሰ ሕዝብ ጋር ይኖር ስለ ነበረ ነው፤ (ይህንም ቀደም ሲል በተመለከትናቸው 5 ምዕራፎች አስተውለናል):: ኢሳይያስ እንደ አይሁድ የረከሰ ነበር ማለት አይደለም፤ ብንወድም ባንወድም በምንኖርበት ኅብረተሰብ ተፅዕኖ ሥር እንኖራለን:: እንደ ኢሳይያስ አገላለጽ የእግዚአብሔርን ቅድስና ባወቅን መጠን ኃጢአታችንን እንገነዘባለን፤ ከኃጢአታችን የምንነጻውም በእግዚአብሔር ምሕረት ብቻ መሆኑን (ቊ. 7) እንረዳለን፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ከማከናወናችን በፊት ከኀጢአታችን የመንጻትን አስፈላጊነት እናስተውላለን::

ቊጥር 8ን እናነባለን፤ ባለፉት 5 ምዕራፎች እንደተመለከትነው፥ እግዚአብሔር መልእክቱን ማራኪ ወዳልሆነው ብዙ ሕዝብ ማን ሊያደርስለት እንደሚችል ሲጠይቅ እናገኘዋለን:: ኢሳይያስ ይህን ተልእኮ በፈቃደኝነት ይቀበላል፤ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ከቊጥር 9-10 ያለውን ቃል ተናገረ፤ ይህ ቃል ባጭሩ ሲጨመቅ ትርጉሙ «አብዝተህ በሰበክህቸው መጠን እነርሱ ደግሞ የበለጠ ለመስማት እምቢ ብለው ጆሮአቸውን ይደፍናሉ፤ ልባቸውንም ስለሚያደነድኑ ንስሐ ገብተው ይቅርታ ለማግኘትም ያስቸግራቸዋል»፤ የሚል ነው::

ይህ ኢሳይያስን የሚያበረታታው ዜና ባለመሆኑ በቊጥር 11 ላይ እንደተጻፈው «ይህ እስከመቼ ይቀጥላል? ለሦስት ወራት? ... ለአንድ ዓመት? ... ለአምስት ዓመት?» በማለት እግዚአብሔርን ይጠይቃል:: እግዚአብሔርም መልሶ «ሕዝቡ እስኪወድቅ፥ ኢየሩሳሌምም እስክትፈራርስና ሕዝቡ በምርኮ ወደ ባዕድ አገር እስኪወሰድ ድረስ እየቀጠለ ይቀጥላል» ይለዋል፤ (ቊ 11-12 ይመ.)::

ነገር ግን ታሪኩ በዚህ ብቻ አይደመደምም:: «በምሕረቱ አዳኝ የሆነው እግዚአብሔር ዐላማውን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ገና እየሠራ ነበር:: ከእነዚህ መካከል ለእርሱ ታማኞች የሆኑትን ለማዳን ተስፋ ይሰጣል፤ ከእነዚህም መካከል ለእርሱ የሚሆነውን አዲስ ሕዝብ ለራሱ ይገነባል::

እግዚአብሔር በማጠቃለያው ክፍል በምሳሌ አስደግፎ ለኢሳይያስ ማረጋገጫ ይሰጠዋል:: በግልጽ እንደሚታየው፥ የሞተ ሕዝብ ተቈርጦ ከወደቀ በኋላ ጉቶው ይቀራል፤ የተቈረጠውም በሚቃጠል ትልቅ ዛፍ ይመሰላል፤ ጉቶው ጨርሶ ስላልደረቀ ትንሽ አረንጓዴ ቅጠሎች በላዩ ላይ ያቈጠቊጣል፤ ያቈጠቈጠው ነገር በኋላ ዛፍ ይሆናል:: ስለዚህ የኢሳይያስ ጥሪት ከንቱ አልቀረም፤ የተወሰኑት

ሰዎች ስብከቱን ሰምተው ይቀበሉታል፤ እነዚህ ጆሯቸውንና ልባቸውን የከፈቱ ሰዎች የእግዚአብሔር እውነተኞች ሰዎች ናቸው። ሲታዩ ብዛታቸው አናሳ ናቸው፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አማኞች የሆኑትን፥ ዘሮቻቸውንም ጠብቆ ያቆያቸውና ከእነርሱ አዲስ ሕዝብ እንዲወጣ ያደርጋል። ኢየሩሳሌም ትጠፋለች፣ ሕዝቡም የሞተና ያበቃለት ይመስላል፤ ቢሆንም እግዚአብሔር በሥራ ላይ ነው።

ኢሳይያስ የዕድሜ ባለጠጋ ሆኖ የሥራውን ውጤት በተከታታዩ ትውልድ ላይ ለማየት እንዳልቻለ ሁሉ፥ እኛም የሥራችንን ፍሬ ለማየት አንታደል ይሆናል። ይህን ክስተት እንደ ፍሬ አልባነት ሳንቈጥር ነቢዩ ኢሳይያስ ተስፋ ሳይቈርጥ፥ ለታዘዘው ተግባር ራሱን በመስጠት የከፈለውን መሥዋዕትነት እንደ አብነት አድርገን ልንማርበት እንችላለን። እርሱን ለአገልግሎት የጠራውና አብርትቶ በሥራ ላይ ያሠማራው አምላክ፥ ዛሬም ቢሆን ሥራውን እየሠራ ለመሆኑ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

### ተጨማሪ ሐሳቦች

በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 1-6 ላይ ያደረግነውን የልምምድ ሥራ ስንመረምር፥ ምንባባችን ከሠላሳ ጥቅሶች በላይ ያካተተና ለሠላሳ ደቂቃ ስብከት በቂ ሐሳብ ቀርቦበታል። በምዕራፍ 1ና3 ላይ ግን ክፍሉን ማስተዋወቃችንን ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ ማንበባችንን፥ ጥቅሶቹ ደግሞ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲገልጹ መተዋችንን ማስታወስ ይገባናል። በእያንዳንዱ ክፍል ላይ እያንዳንዱን ጥቅስ ማንበብ አያስፈልገንም። በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት የመጀመሪያውን ግማሽ ክፍል ብቻ የምናነብ ስንሆን፥ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ሁለተኛውን ግማሽ ብቻ እናነባለን። የበለጠ ማብራሪያ የምንሰጥባቸው ምዕራፍ 5 እና 6 ናቸው። እዚህ ላይ ያሉት ጠቅላላ ቍጥሮች ግን ዐሥራ አምስት ብቻ ናቸው፤ እነዚህ ቍጥሮች በሁለተኛው የስብከቱ አጋማሽ ላይ አብራርቶ ለመስበክ አመቺ ናቸው።

ከፈለግን፥ ወደ መድረኩ ወጥተን የምንሰብክበትን ማስታወሻ በማዘጋጀት ፈንታ፥ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በምንፈልገው ሐሳብ ሥር መስመር ማድረግ እንችላለን። እንዲያውም በኅዳጉ ላይ ቁልቁል መስመሮችን በምንፈልጋቸውና በምናነባቸው ጥቅሶች ቅንፍ ማድረግ እንችላለን፤ በተጨማሪም ደማቅ በሆነ ቀለም በጥቅሶቹ ላይ አስተያየት፥ ማብራሪያ ካለን ብንጽፍ ይቻላል። የምንመርጣቸው አራቱ ክፍሎች በቍጥርና በርእስ ቢለዩ ስብከታችንን በምንቀጥልበት ጊዜ በቀላሉ ሊታዩን ይችላሉ። የራሳችንን የአሰባበክ ስልት ስናዳብር የራሳችን የሆነ መልእክት፥ የመስመር አጣጣልና የቀለም ዓይነት መጠቀሙንም እናዳብራለን። ይህ ልምምድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይ የምንፈልገውን ክፍል ወይም ማስታወሻ ሳንደናገር በቀላሉ ለማየትና ለመጠቀም በጣም ያግዘናል።